ጅማ ዩኒቨርስቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር

# የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ

(በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ወለጋ ዞን በጉደያ ቢላ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ሦስት የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተተኳሪነት)

በ

ከተማሽ የወጉ

ነሐሴ2013 ዓ.ም
ጅማ፣ኢትዮጵያ

# በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ወለጋ ዞን በጉደያ ቢላ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ሦስት የመንግስት የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ

ጅማ ዩኒቨርስቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር

ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

ከተማሽ የወጉ

ዋና አማካሪ፣ጥበቡ ሽቴ ( ዶ/ር )

ረዳት አማካሪ፣ መህረት ሳዳም ( ዶ/ር )


ነሐሴ 2013 ዓ.ም

ጅማ፣ኢትዮጵያ

# ጅማ ዩኒቨርስቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

### የኢትየጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

### የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር

### በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ወለጋ ዞን በጉደያ ቢላ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ሦስት የመንግስት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ

ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ከተማሽ የወጉ

የፈተና ቦርድ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| አማካሪ | ቀን | ፊርማ |
| ______________________ | ______________________ | _____________ |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |
| ______________________ | ______________________ | _____________ |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |
| ______________________ | ______________________ | _____________ |

ነሐሴ2013 ዓ.ም
ጅማ፣ኢትዮጵያ

# ማረጋገጫ

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ በሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ በአማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር በስነ ዘዴ አማርኛን ለማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና ጅማ ዩቨርስቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ----------------------------------

ፊርማ ------------------------------

ቀን -----------------------------------

# ምስጋና

ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ጀምሬ በሰላም እንዳጠናቅቅ ጤና የሰጠኝ አልፋና ኦሜጋ የሆነው ቸሩ ልዑል እግዚአብሔር ስሙ ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን፡፡

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ውድ ግዜአቸውን ሰውተው በየግዜው የማቀርብላቸውን ጽሁፍ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በጥልቅ በማረም ገንቢ አስተያየታቸውንና መረጃዎችን በመስጠት ከፍተኛ ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ መምህሬ እና አማካሪዬ ለዶክተር ጥበቡ ሽቴ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ለማማከር ብልሀታቸውና ለመልካም ትህትናቸው የተለየ አክብሮትና አድናቆት አለኝ፡፡ በተጨማሪም ትልመ ጥናቱን በመፈተን አስፈላጊውን እርማት ለሰጡኝ ለዶክተር ደመላሽ፣ ለዶክተር ምህረት ሳዳሞ ምስጋና ይድረሳቸው፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ ለዘንጊ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ለጉደያ ቢላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ለጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለ ዘ ጠ ነ ኛ ክ ፍ ል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ተማሪዎች እና የአስተዳደር ሰራተኞች እነዲሁም የተለያየ የሀሳብ ድጋፍን በመስጠት ጽሁፉን በመተየብና በማስተካከል ሙያዊ ምክርን በመስጠት ላገዘኝ ባለቤቴ ለመምህር ደረጀ እንኮሳ፣ ለጋሩማ እንኮሳ ፣ ኤቢሳ እንኮሳ፣ ለእህቴ አስማር ተመስገን፣ለልጄ ኤደን ደረጀ እንዲሁም ስማቸውን ላልጠቀስኳቸውና በሀሳብ ለረዱኝ ጓደኞቼ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ትምህርቱን እንድማር እድሉን ላመቻቸልኝ ጅማ ዩኒቨርስቲ፣ትምህርቱን ለሰጡኝ የጅማ ዩኒቨርስቲ የቋንቋ መምህራን ፣የጉደያ ቢላ ወረዳ ትምህርት ቤቶች ጽህፈት ቤት በሙሉ ክፍ ያለ ምስጋና ይድረሳቸው፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በኦሮሚያ ክልል በምሥራቅ ወለጋ ዞን ጉዳያ ቢላ ወረዳ የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ጥናቱ አይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን ንድፋ ገላጭ ሂደትን የተከተለ ነው፡፡ዘጠነኛ ክፍል በአመቺ ንሞና ዘዴ ተመርጧል፡፡በዚህ መሰረት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዋናነት በመምህራን ላይ ትኩረት ያደረገ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ምልከታ ተከናውኗል፡፡በተጨማሪም ለመምህራን ቃለመጠይቅ የተደረገ ሲሆን ተማሪዎችም የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ሦስት የጉደያ ቢላ ወረዳ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና መምህራን በጠቅላይ ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ከየትምህርት ቤቱ አንድ አንድ ክፍል በተራ የዕጣ ንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ከሶስቱም ክፍሎች ዘጠና ተማረዎች በቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ ተመርጠው የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ከምልከታ፣ ከቃለ መጠይቁና ከጽሑፍ መጠይቁ መረጃ ትንተና ውጤት መረዳት እንደተቻለው የተወሰኑ መምህራን የዕለቱን ትምህርት ዓላማ በዝርዝር አለማቅረባቸውን፣ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት በጥንድ ወይም በቡድን ሥራ እንዲታገዝ አለመሞከራቸውን፣ በቋንቋው ተጠቅመው በንግግር ሀሳባቸውን በነፃ የሚገልጹሁ ሁኔታ አለማመቻቸታውን፣የንግግር ማስተማሪያ ደረጃዎችን በተገቢው መንገድ አለማከናወናቸውን፣ ከመማሪያ መጽሐፉ ጎን ለጎን የተማሪዎችን ፍላጎት ሊያነሳሳ የሚችል ክንውን በጥንቃቄ አለመመረጡ፣ የዕለቱ የንግግር ክሂል ትምህርት ግልጽ በሆነና በማይረሳ መልኩ አለመቅረቡ፣ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የመናገር እድል አለመሰጠቱ እና ለመናገር ደፋር ያልሆኑ ተማሪዎችን ለማበረታታት ጥረት አለመደረጉ ተረጋግጧል፡፡ በመጨረሻም ለመማር ማስተማሩ ሂደት እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን አስወግዶ የንግግር ክሂሉን ለማዳበር የትምህርቱ ዓላማ በዝርዝር ለተማሪዎች እንዲቀርብ ቢደረግ፣ተማሪዎች ወደዋናው የንግግር ክሂል ትምህርት ከመግባታቸው በፊት የማነቃቂያ ትምህርት ቢሰጣቸው፣ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መነሻ ያደረገ የንግግር ክሂል ተግባራት ቢቀርብላቸው እና ለልምምድ የሚቀርብላቸው የንግግር ክሂል የትምህርት ክፍለ ጊዜ ከመልመጃዎቹ ስፋት ጋር እየታየ ቢመጠን በማለት የመፍትሄ ሀሳብ ቀርቧል፡፡

# ማውጫ


ይዘት ገጽ

ምስጋና ....................................................................................................i

አጠቃሎ ....................................................................................................ii

ማ ው ጫ....................................................................................................iii

የሰንጠረዥ ማውጫ .................................................................................... vvii

ምዕራፍ አንድ.................................................................................................... 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................................... 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት......................................................................... 3

1.3. የጥናቱ አላማ......................................................................................... 4

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ.................................................................................... 4

1.5. የጥናቱ ወሰን ......................................................................................... 5

1.6.የጥናቱ ዉስንነት.....................................................................................5

ምዕራፍ ሁለት .................................................................................................. 6

ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት.......................................................................................... 6

2.1.1.የንግግር 2.1.ክለሳ ድርሳናት .................................................................. 6

ክሂል ምንነት................................................................................................ 7

2.2. የንግግር ክሂልን የማስተማር አላማ.............................................................. 7

2.3. የንግግር ክሂልን መማር........................................................................... 10

2.4. የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ አቀራረብ........................................................ 11

2.5.የንግግር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት................................................ 12

2.5.1. ታሪክ ነገራ ........................................................................................ 14

2.5.2. ችግሮችን አፍልቆ መፍትሄ መፈለግ ........................................................ 15

2.5.3. ሚና ጨዋታ ....................................................................................... 15

2.5.4. ጭውውት .......................................................................................... 16

2.5.5. ቃላዊ ሪፖርት ..................................................................................... 16

2.5.6.ውይይት.............................................................................................. 17

2.6. የንግግር ክሂል ሲተገበር የሚያጋጥሙ ችግሮች..................................................... 19
2.7.የንግግር ክሂል ሲተገበር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማስወገድ የሚጠቅሙ ክንውኖች............20
2.8. በንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ የመምሩ ተግባር............................................21
2.8.1.በአቀራረብ ደረጃ.............................................................................................. 21
2.8.2.በልምምድደረጃ..............................................................................................22
2.8.3.በአፍልቆት ደረጃ............................................................................................. 23
2.9. የቀደምት ስራዎች ቅኝት.......................................................................................23
ምዕራፍ ሦስት......................................................................................................... 26
የጥናቱ ዘዴ አና ንድፍ ............................................................................................. 26
3.1.የጥናቱ ዘዴ ..........................................................................................................26
3.2.የጥናቱ አካሳይ .....................................................................................................26
3.3. የተጠኝዎች ናሙና አመራረጥ ................................................................................26
3.3.1.የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ..................................................................... 27
3.3.2.የመምህራን ናሙና አመራረጥ............................................................................... 27
3.3.3.የምድብና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ................................................................ 28
3.4.የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ...............................................................................29
3.4.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ........................................................................................ 29
3.4.2. የፅሑፍ መጠይቅ ................................................................................................ 29
3.4.3. ቃለ መጠይቅ..................................................................................................... 30
3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ ...........................................................................................30
ምዕራፍ አራት......................................................................................................... 31
የመረጃዎች ትንተና.................................................................................................. 31
4.1. ከምልከታ ፣ ከጽሁፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..................31
4.1.1 መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ በአቀራረብ ደረጃ ምን ያህል እንደሚተገብሯቸው መፈተሽ........................................................................ 31
4.1.1.1 የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘመግለጫ.........................................................36
4.1.2 .መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርት ሲተገብሩ የልምምዱን ሂደት መመርመር ................................................................................................................... 39

*4.1.2.1.ተማሪዎች የንግግር ክሂል ተግባራትን እንዲለማመዱ ከማድረግ አንጻር*

ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ መግለጫ..........................................46

4.1.3 *.የንግግር ክሂል ትምህርት ሲተገበር በአፍልቆት ወቅት የሚታየውን ውጤት መፈተሽ.................................................................................................. 50*

*4*.1.3.1.ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ ማድረግ አለማድረጋቸውን

ለማወቅ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ ምላሽ የተገኘመግለጫ..........................53

4.2.. *የመረጃዎቹ ትንተና ማብራሪያ* ................................................................58

*4.2.1. የንግግርን ክሂል ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች ክንውን.................................. 58*

*4.2.2. የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ትግበራ.................................... 59*

ምዕራፍ አምስት ....................................................................................... 61

5.ማጠቃለያ ፣መደምደሚያ እና የመፍትሄ ሀሳቦች ........................................ 61

5.1.*ማጠቃለያ* ................................................................................................ 61

5.2. *መደምደሚያ* ........................................................................................... 61

5.3. *የመፍትሄ ሀሳቦች* .................................................................................. 62

ዋቢ መፅሐፍት.............................................................................................. 65

አባሪ አንድ .................................................................................................. 68

አባሪ ሁለት .................................................................................................. 70

አባሪ ሶስት .................................................................................................. 72

# የሰንጠረዥ ማውጫ


ሰንጠረዥ.3.1.በጥናቱ የተካተቱ ትምህርት ቤቶች፣የምድቦች፣የተማሪዎች እና የመምህራን ብዛት የናሙና መጠን እና የምልከታ ጊዜ መግለጫ ........................................................ 27

ሰንጠረዥ 3 2. የተተኳሪ መምህራን ዳራዊ መግለጫ ........................................................ 28

ሰንጠረዥ.4.1.መምህሩ የዕለቱን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ተግባራትን አቀራረብ አስመልክቶ በምልከታ የተገኘን ውጤት የሚያሳይመግለጫ……………………….33

ሠንጠረዥ.4.2.የንግግር ክሂል ተግባራት አቀራረብን በሚመለከት ከተማሪዎች ምላሽ መግለጫ ........................................................................................................................ 37

ሰንጠረዥ 4.3.የንግግር ክሂል ትምህርት የልምምድ ተግባርን የሚያሳይ ከምልከታ የተገኘ መግለጫ ........................................................................................................ 39

ሠንጠረዥ 4.4. የንግግር ክሂል ትምህርት የልምምዱን ተግባር የሚያሳይ ከመከታተያ የተገኘ መግለጫ ........................................................................................................ 42

ሠንጠረዥ 4.5.የንግግር ክሂል ትምህርት የልምምድ ሂደትን በተመለከተ ከተማሪዎች ምላሽ የተገኘ መግለጫ ................................................................................................ 48

ሰንጠረዥ 4.6 .ተማሪዎች በአፍልቆት ወቅት ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ መምህሩ ያመቻቹበትን ሁኔታ ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ **መግለጫ**......................................50

ሰንጠረዥ 4.7 የአፍልቆት ደረጃ የንግግር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎችን ምላሽ የሚያሳይ መግለጫ ........................................................................... 55

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎች ስለ ቋንቋው የተወሰነ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ብቻ ሳይሆን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በማዳበርና በማጎልበት በታላሚው ቋንቋ ጥሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ ይህም ይሆን ዘንድ መምህራን የተለያዩ ክንውኖችን መፈጸም ይኖርባቸዋል Ur(1996፡)፤Shafaat(2018)፡፡ ከእነዚህም ክንውኖች ውስጥ ምንና እንዴት እናስተምር የሚለው ጥያቄ ግንባር ቀደም ሲሆን፣ይህም የይዘት መረጣና የማስተማሪያ ስልት መወሰንን ይመለከታል፡፡ በተለይም ከይዘት መረጣ በኋላ የማስተማሪያ ስልትን መወሰን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡የማስተማሪያ ስልት ተብለው ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ የንግግር ክሂልን ለመተግበር የሚያግዘው ተግባቦታዊ አቀራረብ ሲኖር እደሆነ LittleWood(1981)፣widdowson (1992) & Kumari(2014)ይገልጻሉ፡፡

የአንድ ቋንቋ መምህር ዋናው ትኩረት ተማሪዎች ስለቋንቋው መዋቅራዊ ስርዓት እንዲያውቁ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በቋንቋው ክሂሎችን እዲያዳብሩና የተለያዩ ክንውኖችን በመጠቀም ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ መርዳት እንደሆነ Mc Donough & Shaw(1992) ያስረዳሉ፡፡ሀሳብ በንግግር በሚገለፅበት ወቅት መታየት የሚገባቸውና ከንግግር ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮች አሉ፤እነዚህም ሀሳብን በትክክለኛ የአረፍተ-ነገር አሰካክ መግለፅና የተገለፀው ሀሳብ በንግግሩ ውስጥ ከሚታየው አካላዊ እንቅስቃሴ ጋር የተዛመደ እና የተመጣጠነ መሆን አለበት በማለት Bygate (1987)፣Dedi(2017) ይገልፃሉ፡፡

በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አተገባበርን በሚመለከት ከመምህር መር የመማር ማስተማር ዘዴ ይልቅ ቡድኖችን በተለያየ መልክ በማደራጀት የተለያዩ ተማሪዎች የተለያዩ ሀሳቦችን በማፍለቅ እንዲነጋገሩ ያደርጋል፤ይህ ካልሆነ ግን መምህሩ የሚከተለው መምህር መር የመማር ማስተማር ዘዴ አተገባበር ተማሪዎች ሐሳብን ለመረዳት ብዙ ጊዜያቸውን ያጠፋሉ በማለት Kumari (2014) ይገልጻሉ፡፡

Sesnan (1997) ሲገልፁ በቋንቋ ትምህርት ክፍል የንግግርና የማዳመጥ ክሂል በክፍል ውስጥ ብዙም ትኩረት ያላገኙበት ምክንያት በርካታ ተማሪዎች በሚገኙበት ትምህርት ቤቶች አብዛኛውን ጊዜ ትኩረት የሚያደርጉት በማንበብና በመፃፍ ክሂሎች ላይ ነው፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት የማዳመጥና የንግግር ክሂሎችን መፈተን አስቸጋሪ ነው ከሚል እምነት የመነጨ ነው፡፡ ነገር ግን አንድን ቋንቋ በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ለመገልገል አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ መለማመድና መገልገል አስፈላጊ እንደሆነና ከነዚህ ክሂሎች ውስጥ ለአንዱ ወይም ለሁለቱ ብቻ ትኩረት ሰጥቶ ሌሎችን ችላ ማለት ከቋንቋ ትምህርት አላማ አኳያ የሚጠበቀውን የባህርይ ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም Harmar(1995) በበኩላቸው የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራት ተማሪዎች ራሳቸውን በመግለፅ ችሎታቸውን የሚያሳድጉበት ክሂል ስለሆነና የቋንቋ ትምህርት ዋነኛ አካል በመሆኑ በተገቢው መንገድ ሊሰጥ እንደሚገባ ይገልፃሉ፡፡

ስለዚህ የንግግር ክሂል የማስተማር ስነ-ዘዴ በክፍል ውስጥ ያለው ሂደት በተለይ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ንግግር የራሱ የአከዋወን ሥርዓት ያለው የቋንቋ ክሂል ነው፡፡ እንዲህም ሲባል ተሳታፊዎች ተራ ጠብቀው ይናገራሉ፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይጠቁማሉ፤ለችግራቸውም መፍትሄ ይሰጣሉ፤የንግግርን ግጥምጥምነት ይጠብቃሉ፡፡ በመሆኑም መምህሩ የንግግር ማስተማር ዘዴውን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ሲያስብ ህጉን በጠበቀ መልኩ መረዳትና የተማሪዎችን ዳራ ታሳቢ ማድረግ አለበት በማለት Cook(1989) ይገልፃሉ፡፡

በተለያዩ የመስኩ ምሁራን እንደተገለፀው የንግግር ክሂል ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለመመስረትና አዎንታዊ ተግባሮችን ለማከናወን ጉልህ ድርሻን የሚያበረክት ስለሆነ ክሂሉን ለማጎልበት የሚረዱ ክንውኖችን በማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ በማካተትም ሆነ በክፍል ውስጥ አተገባበሩን በሚመለከት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ምን እንደሚመስል መመርመርና እንከኖችን መጠቆም ይገባል፡፡

በመሆኑም አጥኚዋ የመምህሩን የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነፃነት መግለፅ እንዲችሉ፣አንደበተ-ርዕቱ ተናጋሪዎች እንዲሆኑና፣ በውይይት እራሳቸውን አጉልተው እንዲያሳዩ፣ የራሳቸው ቋንቋ ከሌሎች ቋንቋዎች ጋር ያለውን ልዩነት

መፈተሽ እንዲችሉ እና በተሰማሩበት የሥራ መስክ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል በመምህራን የመታገዙ ጥረት ምን ያህል እንደሆነ መርምራለች።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ለተግባቦት እድገት መሰረቱ ንግግር በመሆኑ በተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች ክሂሉን ተግባራዊ የሚያደርጉ መልመጃዎችን የያዙ የመማር ማስተማሪያ መጽሀፍት ይታተማሉ።እነዚህ የትምህርት መሳሪያዎች ብቻቸውን ለተማሪዎች በቂ አይደሉም ፤አንድን ፅንሰ ሀሳብ በፍጥነት ላያስገነዝቡ ይችላሉ። ስለዚህ ትምህርቱ ውጤታማ የሚሆነው የቋንቋ መምህሩ ከፍተኛ ጥረት ሲታከልበትና ሳይንሳዊ የሆነ የንግግር ክሂል የመማር ማስተማር አተገባበር ስልቶች ተግባራዊ ሲደረጉ እንደሆነ Harmer(1995) ይገልፃሉ።

መምህራን የንግግር ክሂል አተገባበራቸውን በቡድን ከማስተማር ይልቅ በግል ወይም በተናጠል የሚያስተምሩ መሆኑን በመመልከትና፤ አብዛኛዎቹ መምህራን ለንግግር ክሂል የሚመድቡት ጊዜ በጣም አነስተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ ይህንን ክሂል አቅደውና አላማ ነድፈው ሳይሆን ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ እንደሚተገብሩ Bygate(1987)ይገልጻሉ።

የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያተኩሩት በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ የንግግር ክሂል መልመጃዎች ላይ እንጅ ለንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ዘዴ ብዙም ትኩረት ሰጥተው የማያስተምሩ መሆኑን በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ጥናቶች ጠቅሰዋል። እነዚህም ጥናቶች ውስጥ ፣እጅጉ፣2003፣አያልሰው፣2003፣ጥላሁን፣2003) ይጠቀሉሳሉ። ይሁን እንጅ እነዚህ ጥናቶች የተጠኑበት ጊዜና የክፍል ደረጃ ከዚህ ጥናት ይለያል። በተጨማሪም ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ትኩረት በመማሪያ መጽሀፍት የንግግር ክሂል መልመጃዎችና በአፈ ፈት ተማሪዎች ላይ ብቻ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ኢ-አፈ ፈት እና አፈ ፈት ተማሪዎችን ይመለከታል። ስለዚህ አጥኝዋ ለዚህ ጥናት መነሻ የሆናት በስራዋ አለም ባገኘችው ተሞክሮ ለመገንዘብ እንደቻለችው ተማሪዎች በመማር ሂደት ውስጥ በንግግር ክሂል ከሚያሳዩት ደካማ ግብረ-መልስ በመነሳት እና መምህራኑ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡትን የንግግር ክሂል መልመጃዎች ከማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር በማጣመር በአግባቡ መተግበር ወይም አለመተግበራቸውን ለማወቅ ስለተነሳሳች ነው።በዚህ መሰረት ጥናቱ የ9ኛ

ክፍል ተተኳሪ መምህራንና ተማሪዎችን የተመለከተና የሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ እነርሱም፡-

1. የ9ኛ ክፍል መምህራን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አተገባበር ስልት ምን ይመስላል?
2. መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን ሲተገብሩ በልምምድ ወቅት የመምህር ተማሪ ተራክቦው ቅርፅ ምን ይመስላል?
3. የንግግር ክሂል ሲተገበር በአፍልቆት ወቅት የሚታየው ውጤት ምን ይመስላል?

የሚሉትን ጥያቄዎች መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑን አጥኝዋ ስላመነችበት ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ አላማ

የጥናቱ አጠቃላይ አላማ በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ወለጋ ዞን በጉደያ ቢላ ወረዳ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ይህ አብይ አላማም የሚከተሉት ንዑሳን አላማዎች አሉት፡፡ እነሱም፡-

1. የመምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርትን የአቀራረብ ስልትን መፈተሽ፡፡
2. መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን ሲተገብሩ የልምምዱን ሂደት መመርመር፡፡
3. የንግግር ክሂል ትምህርት ሲተገበር በአፍልቆት ወቅት የሚታየው ውጤት መፈተሽ የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

መምህራን የንግግር ክሂልን የክፍል ውስጥ አተገባበር ተረድተው ለትምህርቱ መቃናት አስፈላጊውን ሁሉ ክትትል እንዲያደርጉ ይህ ጥናት ያበረታታል፡፡ ጥናቱም የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንግግር ክሂልን አተገባበር በማወቅ ለተማሪዎቻቸው ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥቆማ ይሰጣል፡፡
2. ለወደፊት የመማሪያ መፅሐፍ ሲዘጋጅ ስለ ንግግር ክሂል አተገባበር ለመማሪያ መሳሪያ አዘጋጆች መረጃ በመስጠት ድጋፍ ይሆናል፡፡
3. በዚህ ጥናት ዙሪያ ምርምር ለሚያከናውኑ አጥኝዎች መነሻ ሀሳብ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለተለያየ  የትምህርት ደረጃ የሚሰጥ ነው፡፡ይሁን እንጂ  ይህ ጥናት የተካሄደው በ2012 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ወለጋ ዞን በጉደያ ቢላ ወረዳ በሚገኙ ሦስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ እነሱም፡- ጉደያ ቢላ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ዘንጊ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው፡፡ ጥናቱም ያተኮረው በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበር ላይ ሲሆን የዚህ ክፍል መምህራንና ተማሪዎች የጥናቱ ተተኳሪ ናቸው፡፡

## 1.6.የጥናቱ ውስንነት

በዚህ ጥናት በስፋት ያልተዳሰሱ ጉዳዮችን ስንመለከት የዚህ ጥናት ውጤት በ2012 ዓ.ም በተከሰተ የጤና ችግር (ኮቪድ-19 በሽታ) ምክንያት ከአጠቃላይ ከታቀደው አስራ ሁለት የምልከታ ጊዜ የተቋረጡ ስድስት የምልከታ ጊዜያት ሲሆኑ በስድስት የምልከታ ጊዜ ብቻ ተተግብሮ የተገኘ ውጤት ከመሆኑ አኳያ ውስንነት ስለሚኖረው ሰፋ ባለ የምልከታ ጊዜና ተመሳሳይ የአጠናን ዘዴን ተከትሎ በመተግበር የመምህራንን የንግግር ክሂል አተገባበር በመፈተሽ የተማሪዎችን የንግግር ብቃት ለማጎልበት ያለውን ሚና በጥልቀት ለማወቅ በቀጣይ ጥናት ማከናወን አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

## 2.1.ክለሳ ድርሳናት

የሰው ልጅ ማንነቱን፣አመለካከቱን፣ስሜቱንና ፍላጎቱን ለሌላ ሁለተኛ ሰው ከሚያስተላልፍበት ተግባቦታዊ ክሂል አንዱ ንግግር ነው፡፡ የንግግር ክሂል ከማዳመጥ ክሂል ጋር በእጅጉ የተቆራኘ እና ምላሽ የሚፈልግ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ንግግርን ለማጎልበት የሚያስችሉ ተግባራት በአብዛኛው ተማሪው ላይ የሚያተኩሩ መሆን አለባቸው፡፡ ንግግርን ማስተማር የሚቻለው መምህሩ ብቻ እየተናገረ ሳይሆን አብዛኛውን የንግግር ጊዜ በመጠቀም ተማሪዎች እየተናገሩ ከንግግራቸው መማር ሲችሉ ነው በማለት Pressley & etal.(2007) ይገልፃሉ፡፡

ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ ንግግር አንዱ ሲሆን ከመጻፍ፣ከማዳመጥና ከማንበብ የበለጠ ለተግባቦት ስራ በጣም አስፈላጊው ክሂል ነው፡፡Ur(1996)ሲገልጹ ንግግር አእምሯዊ ወይም አካላዊ ችግር ከሌለ በስተቀር የማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር መግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡ የንግግር ክሂል ልምዱ የሚጀምረው ከቤተሰብና ከማህበረሰቡ ጋር በሚደረግ መስተጋብር እንዲሁም በትምህርት የሚዳብር ነው፡፡ ይህም ከሌሎች ክሂሎች ማለትም ከማንበብ ከማዳመጥና ከመፃፍ ክሂል የሚለየው ባህሪው ነው በማለት ይገልጻለ፡፡ Lewis and Sick (1983) ይህንኑ ሀሳብ ሲያጠናክሩ ንግግር ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ከፍተኛውን ቦታ የሚይዝ ነው፡፡ አንድ ሰው ቋንቋን አወቀ የሚባለው መናገር ሲችልና በቋንቋው ሀሳቡን መግለፅ ሲችል ነው ይላሉ፡፡

Bygate,(1987) አንድ ሰው ንግግር ይችላል የሚባለው ከአንደበቱ ቅላፄና ምት ያለው ቃላት ማውጣት በመቻሉ ብቻ ሳይሆን ለተነሳበት ጉዳይ የሚውል እና ሀሳቡን በትክክል ሊያስተላልፍለት የሚችል ቃል መምረጥ ሲችል ነው፡፡ በቃላት መረጣ ጊዜም ይህን ቃል በዚህ ሰዓት ብናገረው የአድማጭን ስሜት ሊስብልኝ ይችላል ወይ? የተነሳሁበትን አላማ ሊያሳካልኝ የሚችል ቃል ነው ወይ ? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ይኖርበታል በማለት ገልፀዋል፡፡

በተጨማሪም ከሌሎች የክሂል ዘርፎች ጋር ጥልቅ ግኝኙነት አለው የምንልበት ምክንያት አንዱን ክሂል በምናስተምርበት ጊዜ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ሁሉንም ክሂሎች ለማስተማር ስለምንገደድ ነው፡፡እንዲሁም የንግግር ክሂል ከሌሎች ክሂሎች ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ቢኖረውም  የራሱ የሆነ መለያ ባህሪም አለው፡፡አንድ የንግግር አቅራቢ ስለ አንድ ጉዳይ በሚናገርበት ጊዜ የሚጠቀምባቸው አረፍተ-ነገሮች በአብዛኛው አጫጭር ናቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ የቃላት አመራረጥና የሰዋሰው አወቃቀሩ የተሳካ ይሆናል፡፡

### 2.1.1.የንግግር ክሂል ምንነት

ንግግር ሀሳብ እንደመጣ ማፍለቅ ሳይሆን ሰው የተመለከተውን፣ስሜት ያፈለቀውን፣ በንባብና በማዳመጥ ያገኘውን ሃሳብ መነሻ በማድረግ በቋንቋ ድምጾች አማካኝነት መልዕክትን ለሌላ ወገን በስርዓት ማስተላለፍ መቻል ሲሆን በማህበራዊ ህይወት ውስጥም የጎላ ሚና ይጫወታል በማለት Celce-Muricia & Oishtain(2000)ይጠቅሳሉ፡፡

ንግግር እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ የመግባቢያ መንገድ ነው፡፡በመሆኑም ሰዎች ከመሰሎቻቸው ጋር በሚያደርጉት የመግባባት ሂደት መልዕክታቸውን በሚያስተላልፉበት ጊዜ ስርዓትን ጠብቀው በብቃትና በጥራት ሊገለገሉበት ይገባል በማለት ተስፋዬ(1981)ይገልፃሉ፤፡ እንደ Marriam & etal.(2015) ገለጻ ንግግር ከማንበብና ከመጻፍ ክሂሎች ቀደም ብሎ የሚለመድ ሲሆን የሰው ልጆች የተለያዩ ክስተቶችንና ክንውኖችን ለመግለጽ የሚገለገሉበት መሰረታዊ የቋንቋ ክሂል ነው፡፡ ሰዎች የራሳቸውን ባህልና ማንነት በንግግር አማካኝነት ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም የንግግር ክሂል የቋንቋው ተጠቃሚ ማህበረሰብ በሚፈቅደው መንገድ የራሱ የሆነ ህግና ሥርዓትን የተከተለ ድምጻዊ መግባቢያ ነው፡፡

## 2.2. የንግግር ክሂልን የማስተማር አላማ

Bygate.(1987)፤ Hussein(2018)እንደገለጹት በቋንቋው ለመገልገል የሚያበቃ ክሂል መኖርና የቋንቋ መዋቅርን ማወቅ የመማር አላማን ለማሳካት ይጠቅማል፡፡ የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ ከማስተማር አላማዎች አንዱ ተማሪዎች በተለያዩ አቅጣጫዎች ያላቸውን ተሳትፎ ማጠንከር ነው፡፡

የተማሪዎች የቋንቋ እውቀት የሚመዘነው በታላሚው ቋንቋ ለመማር ፣ለመናገርና ሀሳብ ለመለዋወጥ ያላቸውን ችሎታ በተሳትፎ ማሳደግ ሲችሉ ነው፡፡ተማሪዎች በቋንቋ ክፍለ ጊዜ ንግግር እንዲማሩ ሁኔታዎች ካልተመቻቹላቸው ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት ይቀንሳል፡፡ ስለዚህ መምህራን ንግግር የሚያስተምሩበትን ምክንያት ለይተው ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ የንግግርን ክሂል ለማስተማር ምክንያት ከሚሆኑት ነጥቦች መካከል ተማሪዎች፡-

- ✓ የድምፅ ቅንብሮችና የንግግር ድምፆችን መፍጠር እንዲችሉ፤
- ✓ ቃላትና አረፍተ-ነገሮችን በተገቢው አውድ እና የመነጋገሪያ ርዕስ ዙሪያ መገልገል እንዲችሉ፤
- ✓ የቃላት፣የአረፍተ-ነገር ጥብቀትና ቃናን በቋንቋ መጠቀም እንዲችሉ፤
- ✓ ሀሳብን በቅደም ተከተልና ትርጉማዊ በሆነ መንገድ ማቀናበር እንዲችሉ፤
- ✓ ቋንቋን በፍጥነትና በራስ መተማመን እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡

Paul,Nation.(1990)ተማሪዎች በድግግሞሽ አንድን የተጠና ንግግር ሲለማመዱ እንዴት ክሂላቸውን እንደሚያሻሽሉ ማወቅ ይገባል፡፡ በዚህም ልምድ ተማሪዎች ሰዋሰዋዊ ክሂሎችን ከድግግሞሽ የንግግር ልምምድን ሊያሻሽሉ አንደሚችሉ ይገልፃሉ፡፡ የንግግር ልምምድ በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ብዙ ግቦች አሉት፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡-

- ✓ የትምህርቱን ዋና ሃሳብ ለይቶ ማወቅ፤
- ✓ ከሌሎች ተሳታፊዎች ስለ ቋንቋው አጠቃቀም መረዳት፤
- ✓ ትክክለኛ የቋንቋ አጠቃቀምን ማዳበር፤
- ✓ የንግግር ዘዴዎችን መማር፤
- ✓ የንግግር ክሂሎትን ማዳበር ናቸው፡፡

Harmer.(2007፡123) የንግግር ክሂል ትምህርት ሲተገበር ተማሪዎችም በክፍል ውስጥ እንዲያከናውኑ የሚጠበቅባቸው ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶችን እንደሚከተለው ይጠቅሳሉ፡

የንግግር ክሂል ተግባራት የልምምድ እድሎችን በክፍል ውስጥ ስለሚሰጡ፤
ተማሪዎች የሚገለገሉባቸው የንግግር ክሂል ተግበራት ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎች ግብረ-መልስ በመስጠት ጥሩ መስራታቸውንና ውጤታማ መሆናቸውን ስለሚያሳዩበት፤
ተማሪዎች የቀሰሙትን  የቋንቋ እውቀትና የመጠቀም ችሎታቸውን ስለሚጨምር ነው፡ ፡

በድሉ (2007)ሲገልጹ በሀገራችን አብዛኞቹ ተማሪዎች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁት ጥሩ የንግግር ችሎታ ሳያዳብሩ ነው፡፡ በመሆኑም ከትምህርት ቤት በኂላ ባለው ህይወታቸው ያለምንም ችግር ሀሳባቸውን በንግግር ለመግለፅ ይቸገራሉ፡፡ በራስ ያለመተማመን፤መልዕክትና ውጤት አቀናጅቶ ያለማቅረብና የቋንቋውን ስርዓት ያለመጠበቅ ከሚያጋጥማቸው ችግሮች ወስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ የማስተማር ዋና አላማም እነዚህን ንዑሳን ክሂሎች በማዳበር ተማሪዎች ጥሩ የንግግር ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡

የአፍልቆት ክሂል የሆነውን የንግግር ክሂልን የማስተማር ዋና አላማ የቋንቋ ፍሰትን ወደሚፈለገው ደረጃ ማድረስ እና የስኬታማ ቃላዊ ተግባቦት ክሂልን ማሳደግ ነው፡፡ ቋንቋውን በአግባቡ መጠቀም የንበት፣የሰዋሰው፣የቃላት፣የዲስኩርና ወዘተ..ዕውቀቶች የአፊ-ፊት ተናጋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችም ተግባራት ጭምር ናቸው በማለት በድሉ (2007) ገልፀዋል፡፡

አፊ-ፊትም ሆነ ኢ-አፊ-ፊት የቋንቋ ተናጋሪዎች የቃላትን ንበት ስርዓት ማወቅ አለባቸው፡፡ ይህም እውቀት የድምፅ፣ የጥብቀት እና የቅላፄ ዘርፎችን የሚመለከት ሲሆን የቋንቋው ተናጋሪዎች ድምፆችን ማፍለቅ፣ቃላት የሚጠብቁበትን ቦታ መለየት፤ የተለያዩ ድምጾችን ምንነት መረዳትና መተግበር መቻልን ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

በተጨማሪም Nunan(1994) ሲገልጹ ተማሪዎች ቃላትን በጥሬ ፍቺያቸው ብቻ ሳይሆን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺን በመለየት ምስጥራዊ የቋንቋ አጠቃቀምን መረዳት አለባቸው፡፡ የንግግር ክሂል ማስተማርን Harmer(1995:) ሲገልጹ ተማሪዎች በቋንቋ ተጠቅመው ሀሳባቸውን ማቅረብ እንዲችሉ ዘመናዊ በሆነ የክፍል ውስጥ የመስተማር ዘዴ ትምህርቱ ሊቀርብላቸው ይገባል፡፡የማስተማሪያ ዘዴውም የሚከተሉት ጥቅሞች ይኖሩታል፡፡

- ✓ ተገቢ ቃላትን አንደአስፈላጊነቱ መጠቀም እንዲችሉ ይረዳል፡፡
- ✓ ሀሳባቸውን በማስረጃ አስደግፈው ማቅረብ እንዲችሉ ያግዛል፡፡
- ✓ ሀሳባቸውን ነፃ ሆነው እንዲገልፁ ይጠቅማል፡፡
- ✓ መደበኛ የአነጋገር ስልት እንዲጠቀሙ ይረዳል ፡፡

- ✓ ኢ-አፌ-ፌት ተናጋርዎች ከአፌ-ፌት ተናጋርዎች የንግግር ስልትን እንዲማሩ ይረዳቸዋል በማለት ገልፀዋል፡፡

## 2.3. የንግግር ክሂልን መማር

Harmer(2007)እንደገለጹት የንግግር ክሂል ሀሳብን ለማስተላለፍና ለማብራራት የምንጠቀምበት ክሂል ሲሆን ከማዳመጥ ክሂል ቀጥሎ አብዛኛውን ጊዜያችንን የምናጠፋው በዚሁ ክሂል ነው፡፡ ሰዎች ሁለተኛ ቋንቋቸውን ሲማሩ ማወቅና ይበልጥ መገልገል የሚፈልጉት በንግግር ነው፡፡ በመሆኑም በማንኛውም እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ሰፊ ቦታ የሚሰጠው ሲሆን በተገቢው መንገድና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ማስተማር ተገቢ ነው፡፡ እንዲሁም የንግግር ክሂል የተለያዩ ማህበራዊና ትምህርታዊ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ከእነዚህም ውስጥ፡-

- ✓ በርካታ የቋንቋ እውቀት ለማግኘት ያስችላል፤
- ✓ የንባብና የፅህፈት ክሂሎችን ያሳድጋል፤
- ✓ ተማሪው የሚማረውን ቋንቋ ንበት፣ የድምጾችን አወጣጥ ለማወቅና
- ✓ ላቅ ያለ ማህበራዊ ደረጃ ላይ ለመድረስ ይጠቅማል፡፡

Brum(1984)፣Alumettu(2018)ተማሪዎች የንግግር ክሂልን ሲለማመዱአንደበተ ርዕቱነታቸውን በአግባቡ እያሻሻሉ ይሄዳሉ፡፡ በልምምዱ ወቅትም በየመሀሉ ምን ልናገር ብሎ አያቆምም ወይም እንዴት ራሱን መግለፅ እንዳለበት አይቸግረውም፡፡ ይህ አንደበተ-ርዕቱነት መሰረት የሚያደርገው የቋንቋው የቃላት አገባብ ዘዬዎችን በደንብ መጠቀም በቋንቋው መግባባት መቻልን ያዳብራል፡፡ በመሆኑም የአንድ ተማሪ አንደበተ- ርዕቱነት የሚለካው ቋንቋን ቶሎ በመናገር ፣ የቋንቋው የቃላት አሰካክ፣የቋንቋውን ሂደት የመቆጣጠር ብቃት እና የቋንቋ ሰዋሰዋዊ አገባብን በአግባቡ መጠቀም ሲችል ነው፡፡ በተጨማሪም መምህሩ አንደበተ-ርዕቱነትን ለማሳደግ በልምምድ ወቅት የተለያዩ መልመጃዎችን በትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል በማለት ገልፀዋል፡፡

## 2.4. የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ አቀራረብ

Rechards(1994)፤Benter(2015) እንደገለጹት የንግግር ክሂል አቀራረብ ተማሪዎች በቋንቋ ተጠቅመው ልዩ ልዩ ማህበራዊ አውዶች ውስጥ ሀሳባቸውን ለማስተላለፍ ይረዳቸው ዘንድ በቂ ልምድ ይሰጣቸዋል፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎች የንግግር ችሎታ እንዲጨምር፣ በክፍል ውስጥ ያላቸው የተነሳሽነት ብቃታቸው እንዲያድግና የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እንዲያከናውኑ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡

የንግግር ክሂል አቀራረብ የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ አብዛኛውን ጊዜ ግልጋሎታዊም ሆነ ስነ-ልሳናዊ አላማው ከተማሪው ፍላጎትና ችሎታ አኳያ ይለያያል፡፡ ተግባሩም የሚከናወነው በጥንድ ወይም በቡድን ሀሳብን መረዳት እንዲችሉ፣ እንዲወያዩ፣እንዲከራከሩ ወዘተ.. የሚረዳ ነው፡፡ይህም የንግግር ክሂልን ለማስተማር በከፍተኛ ደረጃ ሁኔታዎችን ያመቻቻል በማለት Rechards (1994) ያስረዳሉ፡፡ እኚሁ ምሁር የንግግር ክሂል አቀራረብ የንግግር ክሂልን ከማዳበር አኳያ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው መሆኑንና የአቀራረብ ስልቱን ሲገልፁ፡-

- ✓ ጭውውቶችን በሚማርክ መንገድ ማቅረብ፤
- ✓ ጥሩ አድማጭና ተናጋሪ መሆን፤
- ✓ የሰዎችን ጥያቄ አገናዝቦ መመለስ፤
- ✓ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን፣ተረቶችን፣አፈ-ታሪኮችን ወዘተ… በንግግር ውስጥ ጣልቃ እያስገቡ መናገር፤
- ✓ በውይይት ፣በክርክር፣ በተለያዩ ምርምሮች ላይ በተወሰነ ርዕስ ላይ መናገር፤
- ✓ **መልዕክት** አስተላላፊውን ሰው በጥንቃቄ በመከታተል መስማማቱን ወይም መቃወሙን፣ ሌሎች መረጃዎች መጨመርን ወዘተ››ያካተተ ጠቀሜታ አለው፡፡

Brown &Yule.(1983) እንደገለጹት አንድ የቋንቋ መምህር ንግግርን ከማህበራዊና ተግባራዊ ማነቃቂያ ጋር አያይዞ ማስተማር ተገቢ ነው፡፡ ተግባራዊ ንግግርን ስናስተምር ተማሪዎች የመረጃ ልውውጥ እንዲያደርጉና እዚያው ክፍል ውስጥ ሊተገበሩ የሚችሉትን ስራዎችን ማከናውን ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ማህበራዊ ግንኙነታቸውን እንዴት አድረገው አንደሚመሰርቱ ማስተማር፤ በክፍል ውስጥም በምን መልኩ እንደሚያከናውኑት ማስተማር፤ ከቤተሰቦቻቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር በውይይት መልክ እንዲተገብሩ ማድረግ ይገባል፡፡በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አራቱን የቋንቋ ክሂሎችን መጠቀም የመምህሩና የተማሪዉ ተግባር ነው፡፡ በተጨማሪም መምህሩ የተለያዩ አዳዲስ መረጃዎችን በመጠቀምና በተቻለ መጠን

በታላሚው ቋንቋ የሚቀርበውን ተግባር ግልፅና በማያሻማ መልኩ ማቅረብ አለበት። በዚህ መልኩ ተግባራዊ ከሆነ ተማሪዎች አዳምጦ መገንዘብና መናገር ይችላሉ። በማለት Byrme (1987) ይገልጻሉ።

## 2.5.የንግግር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት

Harmer(2007)፣Shafaat(2018) እንደገለጹት ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የንግግር ክሂልን ለማጎልበት የክፍል ውስጥ የተማሪዎች ተሳትፎ ወሳኝ ነው።መምህሩ ተማሪዎችን ሊያሳትፉ የሚችሉ የንግግር ክሂል ተግባራትን ማዘጋጀት ይኖርበታል። እነዚህ የንግግር ክሂል ተግባራት ሲዘጋጁ ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፉ ቢሆን ይመረጣል።ይህም የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት ይጨምራል። ተግባራቱም የመረጃ ክፍተት ተግባራት፤ አቅጣጫን ማሰየት፣የስዕሎችን ልዩነት መግለፅ፣በሰንጠረዥ መልክ የቀረቡ መረጃዎችን ማሟላት ላይ ስለሚመሰረት የውስብስብነት በህሪይ አይታይበትም በማለት Harmer(2007)ገልጸዋል።

እነዚህም ባህሪያት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቀላሉ እንዲገልፁ ይረዳቸዋል። ተረቶች (ታሪኮች) ደግሞ የልጅነትን ባህሪ ከመቅረፅ ባሻገር ስሜት የማነሳሳታቸው ደረጃ ከፍተኛ ስለሆነ በክፍል ውስጥ መጠቀሙ ተገቢነት ይኖረዋል። እንዲሁም በድሉ (2007፣92--93) ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የንግግር ተግባር ላይ ከመሳተፋቸው አስቀድሞ ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ቅድመ ንግግር ተግባራት አሉ ይላሉ።እነዚህ የቅድመ ንግግር ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

- ✓ ንግግር የሚደረግበትን ርዕሰ ጉዳይ መወሰን ወይም ፤
- √ በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ መረጃዎችን መሰብሰብ፤
- √ ንግግር የሚደረግበትን ዓላማ ማወቅ፤
- √ አድማጭን መወሰን፤
- √ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ላይ ማስፈርና ቅድመ ተግባራትን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ንግግር ተግባር መግባት የሚሉት ናቸው።

የሚከተሉት ተግባራት ተማሪዎች በንግግር ሂደት ላይ እያሉ ትኩረት ሊያደርጉባቸው የሚገቡ ናቸው።

- √ በንግግሩ መጀመሪያ ርዕሱን ለአድማጭ በሚገባ ማስተዋወቅ፤
- √ የንግግሩን አላማ ባጭሩ ማስተዋወቅ፣
- √ የአድማጭን ስሜትና ፍላጎት መጠበቅ፣

√ አድማጭን በዓይን መቃኘት፣

√ የአድማጮችን ምላሽ መቀበል፣

√ የሚያስፈልጉ መረጃ መሳሪያዎችን መጠቀም፣

√ ንግግሩን ሳቢ አድርጎ ማቅረብ፣

√ የአድማጮችን ጥያቄዎች በማስታዎሻ መያዝ፣

√ ለተጠየቁት ጥያቄዎች ገለፃ መስጠት እና ማጠቃለል፣

√ በንግግሩ መጨረሻ ምስጋና ማቅረብ ፣

የድህረ ንግግር ተግባር ተናጋሪዎች አድማጮቻቸው ምን ያህል መልዕክቱን እንደተረዱ የሚገመግሙበት ነው፡፡ ይህ የተወሰኑትን አድማጮች በዘፈቀደ በመምረጥ የንግግሩን ፍሬ ሀሳብ አስመልክቶ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ለማድረግ ሊካሄድ ይችላል በድሉ (2007)፡፡Ur (1996) ንግግር በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚደረግ የሁለትዮሽ ሂደት ሲሆን ይህንን ክሂል ለማዳበር የሚዘጋጁ መልመጃዎች የመማር ማስተማሩን ሂደት ከመምህሩ መር አቀራረብ በማላቀቅ የተማሪዎችን መስተጋብራዊ ግንኙነት የሚያበረታቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡በመሆኑም ተግባራቱ ተማሪዎችን በጥንድ፤ በሶስትዮሽና በቡድን የሚያሳትፉና በራስ የመተማመን ስሜት በማዳበር ሀሳቦችን እንዲገልፁ የሚያግዙ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የንግግር ክሂል ተግባራትንም እንደሚከተለው አስቀምጠዋል፡፡

**ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ እንዲናገሩ ማድረግ፡-** በተቻለ መጠን ለንግግር ተግባር የተሰጠው ጊዜ በተማሪዎች ንግግር መሸፈን ይኖርበታል፤ ጉዳዩ ግልፅ ሆኖ እያለ ግን የክፍል ውስጥ ክንውን አብዛኛውን ጊዜ በመምህሩ ይሸፈናል፡፡ ስለዚህ የመምህሩን ሚና በመቀነስ መስተጋብራዊ ግንኙነት ጎልቶ እንዲወጣ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ሁሉንም ተማሪዎች ያካተተ ተሳትፎ እንዲኖር ማድረግ፡-** የክፍል ውስጥ ክንውን ጥቂት ቁጥር ባላቸው ተማሪዎች ተፅእኖ ብቻ መወሰን የለበትም፡፡ ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች የመናገር ዕድል ሊሰጣቸው እና ተሳትፎአቸው የተመጣጠነ ሊሆን ይገባል፡፡

**ከፍተኛ ተነሳሶት እንዲፈጠር ማበረታታት-**፡-ተማሪዎች ለንግግር የሚነሳሱት በተመረጠው ርዕስ ጉዳይ ፍላጎት ሲኖራቸውና ሰለ ርዕስ ጉዳዩ የሚናገሩት አዲስ ሀሳብ ስለሚፈጥርባቸው ነው፡፡ ወይም ደግሞ በሂደት ተሳትፎ በማድረግ ለንግግር ተግባር አላማ መሳካት አስተዋፅኦ ለማበርከት ነው፡፡

**የቋንቋ ቅቡልነት ደረጃ፡-**ተማሪዎች ሀሳባቸው ተገቢነት ባለው መንገድ መግባባት መቻላቸውን ወይም የመግለፅ አቅም ያላቸዉ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ መምህራን ከላይ የተጠቀሱትን የስኬታማ የንግግር ክሂል ባህሪያት እና በቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ ክንውን ወቅት መተግበር ከቻሉ ተማሪዎች የንግግር ክሂልን በቀላሉ ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡ከላይ ምሁራን እንደገለፁት የንግግር ተግባር ሲከናወን መምህራኑ ለተማሪዎች ግልፅ የሆነ መመሪያ በመስጠት ክፍለ ጊዜውን ተማሪዎቹ በአግባቡ እንዲጠቀሙበት በማድረግ ማመቻቸት ይኖርበታል፤ከእነዚህም የሚከተሉትን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡

### 2.5.1. ታሪክ ነገራ

Harmer (2007) ሲገልጹ ተማሪዎች ቀደም ሲል የሰሙትን ታሪክ ወይም በራሳቸው የፈጠሩትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው አንዲናገሩ የሚያግዝ ስልት ነው፡፡ስልቱም የተማሪዎችን የመፍጠር ችሎታን ያዳብራል፡፡እንዲሁም ተማሪዎች ሀሳባቸውን መግቢያ፤ሐተታና መደምደሚያን በያዘ ቅርጽ በማቅረብ እንዲለማመዱና የታሪኩን ባህሪያትና መቼት አስመስሎ እንዲያቀርቡ ይረዳል፡፡ሂደቱንም እነደሚከተለው ጠቅሰዋል፡፡

ተማሪዎች በቡድን ይቀመጣሉ ፤ ለእያንዳንዱ ቡድን ተከታታይነት ያላቸው መልዕክት አዘል ስዕሎች ይሰጣሉ ፤ ቡድኖቹ ስዕሎቹን ከተመለከቱ በኃላ ይሰበሰባሉ፡፡ ከዚያም ከመጀመሪያዎቹ ቡድኖች አንዳንድ አባል የያዙ ሌሎች አዳዲስ ቡድኖች ይደራጃሉ፡፡አዲሶቹ ቡድኖችም ቀደም ሲል ያዩአቸው ስዕላዊ መግለጫዎች ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፉ ይናገራሉ፡፡ በመጨረሻም በእያንዳንዱ ቡድን የቀረበው ታሪክ ተመሳሳይ ሀሰብ የያዘ መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ ቡድኖች የየራሳቸውን ታሪክ ለክፍሉ ተማሪዎች ያቀርባሉ፡፡

እንደ Harmer(2007) ተማሪዎች ታሪክ ነንራን እዲለማመዱና እንዲናገሩ በክፈል ውስጥ የሚቀርቡት ተግባራት ለተጠቃሚዎች ህይወት ቅርበት ያላቸው መሆን እንደሚገባቸው ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ ስለልብሳቸው፣ ስለጌጣቸው፣ ስለስዕሎቻቸው፣ ስለትምህርት መሳሪያቸው፣ ስለ አሳለፉት የህይወት ገጠመኝ ወዘተ…እንዲተርኩ የሚያነሳሱ ጥያቄዎችን መምህሩ እንደመነሻ ቢጠቀም ውጤቱ በጣም የተሻለ ይሆናል፡፡

በተጨማሪም Sensnan(1997) ፣Marima (2015) ሲገልፁ ተማሪዎች በሚማሩት ቋንቋ ታሪክ እንዲናገሩ ማበረታታት አስፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ የሚከተሉትን አይነት ታሪኮችን እንዲናገሩ

ማድረግ ጠቃሚነት እንዳለው ጠቁመዋል፡፡ይህም ከዚህ በፊት የሰሟቸውን ታሪኮች ደጋግመው እንዲናገሩ ማድረግ፣የየራሳቸውን ታሪክ እንዲናገሩ ማድረግ ፤ ስላዩኣቸውና ስላከናወኗቸዉ ነገሮች ለክፍል ተማሪዎች እንዲናገሩ እድል መስጠት የንግግር ችሎታቸዉን ለማሳደግ ይረዳል፡ ፡

## 2.5.2. ችግሮችን አፍልቆ መፍትሄ መፈለግ

Bygate.(1987) ሲገልጹ ተማሪዎች ችግሮችን ከሀሳባቸው አፍልቀው የችግሮችን ሁኔታዎች በቡድን የሚመራመሩበት ስልት ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች የተወሰኑ ችግሮችን በማንሳት የችግሩን መፍትሄ ለመስጠት የሚሞክሩበት ሂደት ነው፡፡ በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ያሉትን ችግሮች በማንሳት የወደፊቱን እንዲተነብዩና የሚያመጣውን ችግር እንዲያስቀምጡ፣ እርስ በርስ እንዲወያዩና አንድ ሀሳብ ላይ እንዲደርሱ ያደርጋቸዋል፡፡

በተጨማሪም አንድን ችግር ለመፍታት የሚደረግ የጋራ ውይይት ማካሄድ እንደ ጥሩ ምሳሌ ይወሰዳል፡፡ የዚህ ተግባር ዋና አላማ ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ችግር ከመፍታት ባለፈ ሳይታወቃቸው እርስ በርስ በሚያደርጉት ተግባቦት የንግግር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ሲሆን ለመለማመጃ የቀረበውን ተግባር ለማከናወን ሶስት ደረጃዎች መከተል አስፈላጊ እንደሆነ ይጠቅሳሉ፡፡

የመጀመሪያው አስፈላጊውን መረጃ የመስጫ ጊዜ ሲሆን ሁለተኛው ችግሩን ለመፍታት የሚከናወን ውይይት ነው፡፡ የመጨረሻው ደረጃ ደግሞ የመምህሩ ክትትል ነው፡፡ከላይ ለመጠቆም አንደተሞከረው እንደነዚህ አይነት መልመጃዎች የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ከማዳበራቸው በላይ የተማሪዎችን የችግር ፈቺነት አቅም ያሳድጋል፡፡ በመሆኑም መምህሩ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ ያገናዘቡ መልመጃዎችን መርጦ መስጠትና እንዲለማመዱ ማድረግ አለበት፡፡

## 2.5.3. ሚና ጨዋታ

እንደ Byren(1981)ገለፃ ሚና ጨዋታ ለቋንቋ ትምህርት በጣም አስፈላጊ መሆኑን ስያብራሩ ለመናገር የፈለጉትን ነገር የሚወስኑት ራሳቸው ስለሆኑ መምህራን ምርጫቸውን በመጠበቅ እንዲናገሩ፣ሀሳባቸውን በራሳቸው አገላለጽ እንዲያዳብሩና በተለያየ መልኩ ቋንቋውን እንዲጠቀሙበት ያደርጋል፡፡

Gower,Phllipes,.and Walters.(1995፡105) የሚና ጨዋታን ጥቅም እንደሚከተለው ያስቀምጣሉ::ቀለል ያሉ ሚናዎች ለምሳሌ፡-አቅጣጫን ማሳየት፤እቃዎችን ከሱቅ መግዛትና የመሳሰሉት ዝቅተኛ ዕድሜ ላላቸው ተማሪዎች በጣም አስፈላጊ ሲሆኑ ውስብስብ የሆኑ ሚና ጨዋታዎች ለምሳሌ፡- በአንድ ታሪክ ውስጥ የተካተቱ ገፀ-ባህሪያትን ወክሎ መጫወት አስፈላጊ እንደሆነና የክፍል ደረጃቸው ከፍ ላሉ ተማሪዎች ተስማሚ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

Tricia(1996) አንድን ሚና ወስዶ ተግባራዊ ማድረግ ለንግግር ክሂል በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡ ተግባሩም በጥንድ ወይም በቡድን ቢከናወን የተሻለ ውጤት ያመጣል፡፡ይህም የብዙ ተማሪዎች ተሳትፎ እንዲኖር ያበረታታል፡፡ የሚና ጨዋታ ተግባር በእውነተኛ ህይወት ላይ የተመሰረተ ሁኔታ ከሆነ ልምምዱ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ግልፅና ግብ ያለው ሚና መጫወት ለነፃ ውይይት አላማ አቅጣጫን ያሳያል፤የሚና ጨዋታ ውድድርንና መተጋገዝን ያካትታል በማለት ገልጸዋል፡፡

## 2.5.4. ጭውውት

ጭውውት የንግግር ኪሂልን ለማዳበር ከሚያስፈልጉት ስልቶች ዉስጥ አንዱ ነው፡፡ ተማሪዎች እንደ ክፍል ደረጃቸው የሚቀርብና አስፈላጊ የሆነ የጭውውት ቅንጫቢ መጠቀም ለሚያካሄዱት የጭውውት ተግባር እውነተኛ የንግግር አውድን ያመጣል፡፡ በመሆኑም የሚቀርበው ይዘት ከተማሪዎች ዳራዊ እውቀት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት በማለት በድሉ(2007) ይገልጻሉ፡፡

እንደ በድሉ(2007) ገለፃ ከተማሪዎች ደረጃ ጋር ሲነፃፀር ቀላል የሆነ ርዕስ-ጉዳይ የተመረጠ እንደሆነ፤ ተማሪዎች ጭውውቱን የሚያካሄዱት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው፤ ስለጉዳዩ ያላቸውን ዕውቀትና አመለካከት ለመግለፅ ሳይሆን፤ በመምህሩ ስለታዘዙ ብቻ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የተመረጠው ርዕስ ጉዳይ ከተማሪዎች ደረጃ በላይ ከሆነ ደግሞ ፤ተማሪዎቹ ስለጉዳዩ የሚኖራቸው ዕውቀት አነስተኛ ስለሚሆን የሚናገሩት እጅግ የተወሰነ ነገር ይሆናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች የሚናገሩት ነገር ላይ ጥርጣሬ እንዲኖራቸውና በራስ የመተማመን ደረጃቸው ዝቅ እንዲል ያደርጋል፡፡

## 2.5.5. ቃላዊ ሪፖርት

እንደ በድሉ ዋቅጅራ (2007) አገላለፅ ይህ ዘዴ ተማሪዎች ያነበቡትንና ያዳመጡትን ጉዳይ በራሳቸው የቃላት አጠቃቀምና የአገላፅ ችሎታ በንግግር የሚያቀርቡበት ስልት ነው፡፡

ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ቃላዊ ሪፖርት በሚያደርጉበት ጊዜ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር መምህራን የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡ እነርሱም፡-

- ✓ ከክፍለ ጊዜው አስቀድሞ ተማሪዎች በቂ ዝግጅት ማድረጋቸውን ማረጋገጥ፤
- ✓ ሪፖርቱ ከቀረበ በኋላ አድማጮች ያልገባቸውን ጉዳይ እንዲጠይቁ ማድረግ፤
- ✓ አቅራቢው ለተጠየቀው ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥ ማበረታታት፤

### 2.5.6.ውይይት

Gower,Phllipes.&.Walters(1995) ተማሪዎች አንድ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ፤ ሀሳብን በጋራ እንዲካፈሉ፣በቡድን ሆነው መፍትሔ እንዲፈልጉ ወዘተ.. ሊወያዩ ይችላሉ፡፡ከውይይቱ በፊት ዓላማው በመምህሩ ሊገለጽ ይገባል፡፡በክፍል ውስጥ ከተማሪዎች ጋር የሚደረግ ውይይት ውጤታማ የሚሆነው እነዚህን ነጥቦች ማወቅ ሲችሉ ነው፡፡በማለት የሚከተሉትን ነጥቦች ያስቀምጣሉ፡፡ እነሱም፡-

- ✓ ተማሪዎች በሚናገሩት ርዕሰ ጉዳይ ላይ የመነጋገር ስሜት ሲኖራቸው፤
- ✓ ተግባሩ በአደረጃጀቱ የመናገር ፍላጎት ለመፍጠር በቂ የሆነ የማነሳሳት አቅም ሲኖረው፤
- ✓ ተማሪዎች ለውይይት የቀረበውን ጉዳይ መግለፅ የሚያስችል የቋንቋ ችሎታ ሲኖራቸው
- ✓ ተግባሩ በሚፈልገው አግባብ መሄድ ሲችል ወዘተ...ናቸው፡፡

በድሉ(2007) በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ውይይቶች ተማረዎችን በማነሳሳት ንቁ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ለማድረግ ከእድሜያቸውና ከችሎታቸው ጋር የሚጣጣም የመወያያ ይዘቶችን ማዘጋጀት ተገቢ ነው ይላሉ፡፡ ከዚህ አኳያ ውይይትቶችን ለማነሳሳት ጠቃሚ መንገዶች ናቸው ብለው ከጠቀሷቸው ይዘቶች መካከል የሚከተሉትን ያስቀምጣሉ፡፡

**አባባሎችን ማሻሻል፡-** ለተማሪዎች በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የአከራካሪ አባባሎችን ዝርዝር መስጠትና በቡድን ተወያይተው ማሻሻያ እንዲሰጡ ማድረግ ለምሳሌ፤ወላጆች ወንድ ልጆቻቸውን እንጀራ ማስጋገር፤ ሴት ልጆቻቸውን ደግሞ እንጨት ማስፈለጥ አለባቸው፡፡

**አባባሎችን መቃወም**፡-የተለያዩ አከራካሪ ሀሳቦችን ለተማሪዎች በቁራጭ ወረቀት ላይ በመስጠት መቃወሚያ ሀሳብ እንዲያዘጋጁ ጊዜ መስጠት ከዚያም ከመካከላቸው አወያይ መምረጥና እያንዳንዱ ተማሪ የመቃወሚያ ሀሳብ በየተራ እንዲያቀርቡ ማድረግ አለባቸው;;ከላይ የንግግር ክሂል ለማለማመድ ይረዳሉ ተብለው ከቀረቡት ተግባራት በተጨማሪም Harmer(2007) ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማለማመድ የሚችሉ ተግባራትን ሲገልፁ፡-

- ተማሪዎች የሚፈልጉትን ርዕስ በመምረጥ እርስ በርስ ቃለ-መጠይቅ እንዲያደርጉ ማበረታታት አለባቸው፡፡
- ተማሪዎች የተለያዩ መረጃዎችን ሰብስበው በማደራጀትና በመለማመድ በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ማድረግ ወይም በቤታቸው ያነበቡትን ቅንጫቢዎች ወይም ሙሉ ስራ በንግግር እንዲያቀርቡ ማድረግ፤

ተማሪዎችን በቡድን ከሚደግፉት ሀሳብ አንፃር ወግነው ወይም ሌላውን ቡድን ተቃውመው እንዲከራከሩ ማድረግ የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር ጥሩ የክፍል ውስጥ ተግባር ሲሆን ከንግግር ችሎታ በተጨማሪ  የነገሮችን ተጠየቃዊ ግንኙነት የመመርመር ችሎታም ያዳብራሉ፡፡

ከላይ በተለያዩ ምሁራን የቀረቡት ነጥቦች እንደሚያመለክቱት በነጥብነት የቀረቡት ተግባራት የንግግር ክሂልን ለማለማመድ ተገቢነት አላቸው ወይስ የላቸውም በሚለው ላይ ትኩረት መስጠት እንዳለበት መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የትኞቹ ተግባራት ለየትኞቹ የክፍል ደረጃ ይመጥናሉ ብሎ ማሰላሰል ተጨማሪ የትኩረት ነጥብ ነው፡፡ ስለዚህ ከላይ የቀረቡትን የንግግር ክሂል መልመጃዎች ከተማሪዎች ዕድሜ ፣የክፍል ደረጃ ፣አካባቢ ወዘተ…ጋር በማጣጣም ተግባራቱን መጠቀም እንደሚቻል መምህራን  ሊገነዘቡት ይገባል፡፡ ነፃ ውይይት የንግግር ለዛን ለማዳበር መልካም አጋጣሚዎች መፍጠር ይችላል፡፡ በተለያየ ጊዜ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማድረግ የንግግር ችሎታቸውን ሊያሳድጉ ይችላሉ፡፡

Taricia(1996) ነፃ ውይይት ተማሪዎች ለምልልስ አስፈላጊ የሆነ ቋንቋ እንዲጠቀሙ ያበረታታል፤በሌላው ተናጋሪ ላይ በተወሰነ ጊዜ ምስል እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በርግጥም ነፃ ውይይት ከሌሎች ተግባራት በተሻለ ሁኔታ የበላይነትን ይይዛል፡፡ይሄውም ለተማሪዎች ለእርስ በርስ ውይይት አጋጣሚዎችን ይፈጥራል በማለት ገልፀዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት አንድ የአማርኛ ቋን ቋ መምህር የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ ሲተገብር ሲያስብ ሊያከናውናቸው የሚገቡ በመሆናቸው እነዚህንም ተግባራት በመጠቀም መምህሩ ተማሪዎችን በሚገባ ማለማመድ ይጠበቅበታል፡፡በመሆኑም ይህ ጥናት በተተኳሪዎቹ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት መምህራን መተግበር አለመተግበራቸውን ፈትሿል፡፡

## 2.6. የንግግር ክሂል ሲተገበር የሚያጋጥሙ ችግሮች

Ur(1996)Marimam.(2015) እንደገለፁት የመማር ማስተማር ተግባር በሚከናወንበት ወቅት ተግባሩን የሚያደናቅፉ ሂደቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡የመመህሩ የማስተማር ብቃት ማነስ ፣የዝግጅት ማነስ ፤ የክፍል አመራር ችሎታ ማጣት ወዘተ..ሊጠቀሱ ሲችሉ፣ በተማሪዎች በኩል ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል ደግሞ ዋና ዋናዎቹ ዝም ማለት፣ ተሳትፎ አለማድረግ፣ የሚናገሩትን ነገር ማጣት፣ዝቅተኛ ተሳትፎ ማድረግ ናቸው፡፡ እነዚህም እንደሚከተለው ይብራራሉ፡፡

**ዝም ማለት፡-** የሚናገረው ሰው ከሚያዳምጥ፣ ከሚያነብ ወይም ከሚፅፍ ሰው የበለጠ የሌሎችን ትኩርት ይስባል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ እንሳሳታለን በሚል የፍርሀት ስሜት ስለሚያድርባቸው ከመናገር ይቆጠባሉ፡፡በተጨማሪም ትችቶችን በመፍራትና ንግግራችን የሌሎችን ስሜት መሳብ አይችልም በሚል እሳቤ ሀሳባቸውን በውስጣቸው ደብቀው የመያዝ ባህሪይ ስለሚታይባቸው በክፍል ዉስጥ ለመናገር አይፈልጉም፡፡

**የሚነገር ነገር ማጣት**፡- ለንግግር በተመረጠው ጉዳይ ላይ በቂ መረጃ ስለማይኖራቸው መናገር ቢፈልጉ እንኳን ለመናገር አይደፍሩም፡፡ ተማሪዎች ለንግግር በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በቂ ዳራዊ እውቀት ከሌላቸው የንግግር ግላዊ ፍላጎትና ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡ ይህ አይነቱ ሁኔታ ከተከሰተ ተማሪዎች ለንግግር ጥላቻን እያዳበሩ ይመጣሉ፡፡

**ዝቅተኛ ወይም ሁሉን ያላካተተ ተሳትፎ፡-** አብዛኛውን ጊዜ የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራትን በአንድ ጊዜ የሚያሳትፉት አንድ ተማሪ ብቻ ነው፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ በርካታ ተማሪዎችን በንግግር ተግባር ላይ ማሳተፍ ለቋንቋ ትምህርት ከተመደበው ጊዜ ጋር ሊጣጣም የማይችል ተግባር ነው፡፡ ይህ ሁኔታም የተወሰኑ ተማሪዎች የክፍል

ውስጥ የንግግር ተግባርን በመቆጣጠር የሌሎች ተሳትፎ ውስን እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## 2.7.የንግግር ክሂል ሲተገበር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማስወገድ የሚጠቅሙ ክንውኖች

Ur(1996)፣Kedir,A.(2017)የንግግር ክሂልን በማስተማር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማስወገድ ይረዳሉ በማለት የሚከተሉትን ነጥቦች ጠቅሰዋል፡፡ እነርሱም፡-

**የቡድን ስራ መጠቀም፡-** የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራትን ተማሪዎች በቡድን ሆነው እደንዲያካሄዱ ማድረግና ማለማመድ የሚናገሩ ተማሪዎች ጭምት ተማሪዎች በአራትና አምስት ተማሪዎች አድማጭነት ንግግር እንዲለማመዱ እድል ይሰጣል፡፡ ስለዚህ የሁሉንም ተማሪዎች ተሳትፎ ለማጎልበት መምህራን ትኩረት ቢሠጡት ተመራጭነት አለው፡፡

**ተግባሩ በቀላል ቋንቋ እንዲቀርብ ማድረግ፡-** ተማሪዎች የአንዳንድ ሰዎችን የንግግር ስልት እንደ ምሳሌ ወስደው ለመናገር የሚሞክሩበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህም ሁኔታ ሊያስተላልፉት የፈለጉትን መልእክት ሙሉ በሙሉ ላያስተላልፍ ይችላል፡፡ስለዚህም ተማሪዎች ሀሳባቸውን በራሳቸው የቃላት አጠቃቀም፣በቀላል ቋንቋና የአገላለጽ ችሎታ ተጠቅመው እንዲያቀርቡ ማድረግ በራስ የመተማመን ደረጃቸውን ከፍ በማድረግ የንግግር ክሂላቸውን ያዳብራል፡፡

**የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ሳቢና አነቃቂ ርዕስ መምረጥ**፡-ለተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባር የሚመረጥ ርዕስ ወይም ሳቢ፣ተማሪዎችን ለንግግር የሚያነሳሳና ሊያሳትፍ የሚችል ሀሳብን የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

ርዕሱ የተመረጠው ወይም መልመጃው የተዘጋጀው የተማሪዎችን ፍለጎት መሰረት አድርጎ ከሆነ የተማረዎችን ተሳትፎ ይጨምረል፡፡ ስለዚህ የንግግር ክሂልን የክፍል ውስጥ ክንውን ውጤታማ ለማድረግ በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተራክቦ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ችግሮችን ለመቀነስ ከላይ በመፍትሄነት የቀረቡትን ነጥቦች መምህራን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡

## 2.8. በንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ የመምሩ ተግባር

Nunan (1995)፤Byme(1987)የበርካታ መምህራን አላማ ቋንቋን በማስተማር ሂደትት ክክለኛውን ስልት መከወን ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን ከዘመኑ የንግግር ክሂል ማስተማሪያ ስልቶች ጋር መተዋወቅ አለባቸው፡፡የንግግር ክሂልን ከፅሁፍ ክሂል ጋር እያነፃፀሩ ለማስተማር በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ትኩረት ሰጥተው መመልከት እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

- ✓ የንግግርና የፅሑፍ ቋንቋ ልዩነት አላቸው?
- ✓ ተስማሚ የሆነውን የንግግር ቋንቋ የማስተማር ቅርፅ ወይም ሞዴል የትኛው ነው?
- ✓ የንግግር ክሂልን በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ሲያከናውኑ ስህተት አንዱ የመማሪያ መንገድ
- ✓ መሆኑን ተረድተው በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ነፃ ሆነው እንዲናገሩ ማበረታታት፣
- ✓ ለንግግሩ ተግባር የተማሪዎችን ትኩረት መሳብ የሚችል ፍንጭ መስጠት፣
- ✓ የተማሪዎች አቀማመጥ ለንግግር ተግባራት አመቺ እንዲሆን ማድረግ፣
- ✓ በቡድን ወይም በተናጠል ስራ ውስጥ መምህሩ እየዞረ በመከታተል ማበረታቻ መስጠት፣
- ✓ የንግግር ክሂልን ትምህርት ካከናወነ በኂላ ከተማሪዎች ምጋቤ-ምለሽ ለማግኘት የተለያዩ መጠይቆችን በማደራጀት ማስሞላት፣
- ✓ ንግግሩ የተማሪዎችን ትኩረት መሳብ የሚችል ፍንጭ መስጠት በማለት ገልጸዋል፡፡

Byrne (1976) የአንድ ቋንቋ መምህር ተግባር በክፍል ውስጥ የተሻለ የመማር ማስተማር ሁኔታዎችን መፍጠር ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ተግባር በተጨማሪ አንድ መምህር በንግግር ክሂል አተገባበር የተለያዩ ደረጃዎች የሚከተሉት ሚናዎች እንዳሉት ይገልፃሉ፡፡ እነዚህም ደረጃዎች :-

### 2.8.1.በአቀራረብ ደረጃ

በአቀራረብ ደረጃ መምህሩ የተማሪዎቹን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ተግባራት መምረጥና የተመረጡትን ይዘቶች ግልፅነትና አይረሴነት ባለው መንገድ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ ደረጃ ብዙ ጊዜ ማጥፋት ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ቋንቋውን የሚለማመዱበትን ጊዜ ስለሚያሳጣ ተገቢነት የለውም፡፡

Byrne(1976)እንደሚያስረዱት በዚህ ደረጃ የንግግር ትምህርቱ በምንባብ መልክ ወይም በምልልስ መልክ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ለምሳሌ መምህሩ ውይይቱን በማስተማሪያነተ ለመጠቀም ከፈለገ በቅድሚያ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ሰዎች ሲወያዩ የሚያሳይ ይዘት ማቅረብ ወይም ከዕለቱ ምንባብ ርዕስ ጋር የተያያዙ አጫጭር ምንባቦች በማምጣት ሊያቀርብ ይችላል፡፡ መምህሩ በዚህ ደረጃ የሚያቀርበው አዲስ የንግግር ትምህርት ከሁለት መመዘኛ አንፃር ሊመለከት ይገባል፡፡ የመጀመሪያው በዚህ ደረጃ ብዙ ጊዜ ማጥፋት የማያስፈልግ በመሆኑ ጊዜ መቆጠቡን፣ ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች ቀጣይ የሚቀርበውን የትምህርት ይዘት ክንዋኔዎች እንዲፈጽሙ የሚያስችላቸው ነውን? የሚለውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 2.8.2.በልምምድ ደረጃ

ይህ ደረጃ ተማሪዎች አብዛኛውን የንግግር ተግባር የሚያከናውኑበት ነው፡፡ የመምህሩ ተግባር ልምምዶችን በተቻለ መጠን ማዘጋጀትና ማቅረብ ነው፡፡ልምምዶቹም ትርጉም ያላቸውና አይረሴነት የሚፈጥሩ ሊሆኑ ይገባል፡፡መምህሩ ብዙ ከመናገር በመቆጠብ ተማሪዎች በልምምዱ እንዲሳተፉ እድል መስጠትና አፈፃፀማቸው አጥጋቢ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል፤

Byrne(1976) በዚህ ደረጃ ተማሪዎች በቀረበላቸው አውድ ላይ ተመርኩዘው የማስመሰል እና የመደጋገም ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡በዚህም ጊዜ በቡድን መስራት፣ ከፍተኛ ልምምድ፣ቀጣይነት ያለው ቃላዊ ተግባር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህ ዓላማ የሚያገለግሉ ተግባራት ድምፅን ከፍ አድርጐ ማንበብ፣ የተለያዩ መረጃዎችን እንዲያከናውኑ ማድረግ፣ የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማድረገ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን ክሂል የመለማመድ ተግባራትን ሲገልፁ፡-

***ገምተው እንዲናገሩ የሚያስችሉ መልመጃዎች፡-*** ለተለያዩ ተግባቦታዊ ተግባራት መሰረት የሆኑት ቀለል ያሉ የመረጃ ክፍተት በተለይም ጨዋታዎች ለዚህ ተግባር ማሳኪያ ሊውሉ ይችላሉ፡፡

***መላምታዊ ሁነቶች፡-*** እንዲህ አይነቱ ነገር ቢያጋጥማችሁ ምን ታደርጋላችሁ? በማለት በጉዳዩ ላይ እንዲነጋገሩ ማድረግ፤ ለምሳሌ፡- ብዙ ሚሊዮን ብር ሎተሪ ቢደርሳችሁ ገንዘቡን ምን ታደርጉበታላችሁ?

***ክፍት መልሶች፡-*** ለተማሪዎች የመነሻ ሀሳቦችን ሰጥቶ ሀሳቡን በተለያየ መንገድ እንዲያሟሉ ማድረግ ወዘተ… ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

### 2.8.3.በአፍልቆት ደረጃ

በዚህ ደረጃ የንግግር እድል ለተማሪዎች በመስጠት ቋንቋውን በራሳቸው እንዲጠቀሙና ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ መምህሩ ማድረግ ይገባዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ጊዜ የተማሪዎችን ልምምድ የሚቆጣጠርበትና እንደ ተማሪዎቹ ፍላጐት እንደሚጠይቁት ጥያቄ ሁኔታ የተለያዩ እርዳታዎችን የሚያደርግበት እና ምክር የሚለግስበት ወቅት ነው፡፡ አብዛኛውን ተግባር መምህራን በጥሩ ሁኔታ ካቀረቡና ተማሪዋችን ካለማመዱ በኋላ ሥራቸውን እንደጨረሱ አድርገው ይቆጥራሉ፡፡

Byrne.(1987) ተማሪዎች ነፃ ሆነው ሀሳባቸውን እንዲያስተላልፉ የሚያደርጉበትና ተማሪዎች ምን ያህል መሻሻል እንዳሳዩ የሚከታተሉበት መሆኑን መረዳት አለባቸው፡፡በተጨማሪም ተማሪዎች የራሳቸውን የቃላት እና የሰዋሰው አውቀት በመጠቀም አፍልቀው የሚገልጹበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡በመሆኑም ውይይቶችና ክርክሮችን በማደራጀት በስዕሎች፣በፎተግራፎች፣በካርታዎች ወዘተ...ላይ ተንተርሰው ሀሳባቸውን እንዲያስተላልፉ ማበረታታት ይኖርባቸዋል በማለት ገልፀዋል፡፡

በአፍልቆት ደረጃ ዋናው ትኩረት ተማሪዎች በቀላሉ እና በነፃነት የሚግባቡበትን አውድ መፍጠር እንዲሁም በጋራ የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸተ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ የክፍሉ ተማሪዎች በተወሰነ ቡድን መከፋፈል ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥራቸው የሚበዛ ከሆነ የቡድን ስራ ተመራጭነት ያለው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ደረጃ የቡድን ሥራ መጠቀም ተማሪዎች ሀሳብ ለሀሳብ ለመለዋወጥ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡ በአጠቃላይ አላማችን የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ማዳበር እስከሆነ ድረስ ሁልጊዜ እነዚህን ሦስት ደረጃዎች መጠቀም ይገባናል በማለት Byrne (1986) ይገልፃሉ፡፡

## 2.9. የቀደምት ስራዎች ቅኝት

መምህራን የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማሳደግ ተገቢነት ያላቸውን የንግግር ክሂል ተግባርና ለክፍል ደረጃቸው ተመጣጣኝነት ያላቸውን ይዘቶች በማቅረብ ማለማመድ ይኖርባቸዋል፡፡ በልምምዱ ጊዜም መምህራን ብዙ ከመናገር መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡የተግባራቱ ቀስቃሽና አጓጊ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም አዘውትረው ከተማሪዎች ጋር መስተጋብርን ማድረግ

አይጠበቅባቸውም፡፡ተማሪዎችም የተሰጣቸውን ተግባራት ለመወጣት በጥንድና በቡድን በመሆን ንግግር ያደረጋሉ፡፡የዚህ የቀደምት ጥናት አላማ ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸውን የቀደምት ጥናት ስራዎች መቃኘት ነው፡፡እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

አንደኛ እጅጉ ይማም ‹‹በደብረ ብርሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረብ ግምገማ›› በሚል ርዕስ በ2003 ዓ.ም ለ2ኛ ድግሪ ማሟያ ያደረገው ጥናት ነው፡፡የዚህ ጥናት አላማም በተጠቀሰው ክፍልና ትምህርት ቤቶች የመምህራን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አተገባበርን መመርመር ነው፡፡ጥናቱ የተከተለው አይነታዊና መጠናዊ ምርምርን ሲሆን አቀራረቡም ገለጻዊ ዜደ ነው፡፡ የጥናቱ አቅራቢም በግኝቱ የተማሪዎችን የመናገር ክሂልን ለማሳደግ የቡድን ውይይት ፣ የግል ሥራ ፣ የጥንድ ትግበራ ወዘተ…ማቅረቢያ ዘዴዎችን መምህራን መተግበር አለመቻላቸውን፤ የተማሪዎች ተራክቦ እኩል እንዳልሆነና የተማሪዎች የእርስ በርስ ግንኙነት አቀራረብ ጉልህ ድርሻ የሌለው እንደሆነ ፤ የመምህሩ የመማር ክሂል አቀራረብ ሁሉንም ተማሪዎች አሳታፊ አለመሆኑንና ተማሪዎች ሀሳብ የማፍለቅ ችግር እንደሚታይባቸው የጥናቱ መረጃ እንደሚጠቁም አስረድቷል፡፡

ሁለተኛ አያልሰው ይታየው ‹‹ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ ትምህርት መፅሐፍት ውስጥ የሚገኙ  የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተና ግምገማ›› በሚል ርዕስ በ2003 ዓ.ም ለ2ኛ ድግሪ ማሟያ የተደረገ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ አላማም ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ ትምህርት መፅሐፍት ውስጥ የሚገኙ  የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ይዘቶች የተማሪዎችን የመናገር ክሂል የሚያዳብሩ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን መፈተሽ ሲሆን በ1998 ዓ.ም. የተዘጋጀውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት መሰረት ያደረገና የፍትነታዊ የምርምር ዘዴን (Expermental research) የተከተለ ነው፡፡የዚህ ጥናት አቅራቢ በመፅሐፍቱ ውስጥ የሚገኙ የንግገር ክሂል መልመጃዎች ከተሰጠው ክፍለ ጊዜ ጋር ተመጣጣኝ ያለመሆን፤ክሂልን ከሌሎች የተለያዩ ዜዴዎች ማለትም ፡ -ጭውውት፤ሥዕሎችን፤ክርክሮችን ወዘተ…አለመጠቀማቸው ፤ የንግግር ክሂል መልመጃዎች አዘገጃጀትና መርሆችን አስመልክቶ ችግር ያለባቸው ሆነው ተገኝተዋል በማለት አስረድቷል፡፡

ሶስተኛ ጥላሁን ከበደ‹‹የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አተገባበር ፍተሻ›› በሚል ርዕስ በ2003ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ለሁለተኛ ድግሪ

ማሚያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ በሰሜን ወሎ ዞን በተመረጡ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ቅንጅታዊ የክፍል ዉስጥ አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱም አይነታዊና መጠናዊ ምርምርን የተከተለ ሲሆን አቀራረቡም ገለጻዊ ዘዴ (Descriptive method) ነው፡፡

የዚህ ጥናት አቅራቢ እንደገለጸው መምህራን በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን መልመጃዎች ለመጨረስ እንደሚሯሯጡ፤ከተማሪዎች የሚቀርቡትን ጥያቄዎች ወደ ሌሎች ተማሪዎች መልሰው ከማወያየት ይልቅ መምህራን እራሳቸው ሰፋ ያለ መብራሪያ እንደሚሰጡ፣ መምህራን በተለያዩ ስልቶች አማካኝነት የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅተው ማለማመድ ጊዜ ማጥፋት እንደሆነና ብዙ የተማሪ ቁጥር ባለበት ክፍል መተግበር አስቸጋሪ ነው ብለው ስለሚያስቡ፤ክሂሎችን ለማቀናጀት፤ አጋዥ መሣሪያዎችን ማለትም ክርክሮችን፤ ጭውውቶችን፤ ታሪኮችን መናገር ወዘተ..የማይጠቀሙ መሆኑን አስረድቷል፡፡

ስለሆነም ይህ ጥናት ከቀዳሚዎቹ ከእጅጉ ይማም እና ከአያልሰው ይታየው ጥናቶች ጋር በአጠናን ዘዴው ተመሳሳይ ቢሆንም በአላማ፣በቦታና በክፍል ደረጃ ይለያል፤በተጨማሪም የአያልሰው ይታየው የጥናት  ስራ በመጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የልቦለድ ይዘቶች የንግግር ክሂልን ማዳበር እና አለማዳበራቸውን መፈተሽ የሚል በመሆኑ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ የጥላሁን ከበደ የጥናት ሥራ ደግሞ የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብን የሚመለከት በመሆኑ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡ሌላው እነዚህን የጥናት ሥራዎች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው የንግግር ክሂል አተገባበርን መፈተሽ የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ በመያዛቸው ነው፡፡ ሆኖም ግን ከላይ ያየናቸው ጥናቶች የትኩረት አቅጣጫ አፈ-ፈት ተማሪዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ሁሉንም አፈ-ፈትና ኢ-አፈ-ፈት ተማሪዎችን መነሻ ያደርጋል፡፡እንዲሁም መምህራን ተማሪዎችን እንዴት ያስተምሯቸዋል? የሚለውንም ፈትሿል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ዘዴ እና ንድፍ

### 3.1.የጥናቱ ዘዴ

በምዕራፍ አንድ ለመግለጽ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ትኩረት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የመረጃ ምንጮች አመራረጥ፣የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አይነትና አደረጃጀት፣ የመረጃ አሰባሰብ ሂደትና የጥናቱ አጠናን ስልት በዝርዝር ቀርቧል፡፡ ጥናቱም የተከተለው በአይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴ ሲሆን **አቀራረቡም ገለፃዊ ንድፍን** (Descriptive Method) የተከተለ ነው፡፡

### 3.2.የጥናቱ አካላይ

ጥናቱ የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ወለጋ ዞን በጉደያ ቢላ ወረዳ በሚገኙ ሦስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ ነው፡፡ የተመረጡት ትምህርት ቤቶችም ጉደያ ቢላ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ጀሬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ዘንጊ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው፡፡ ጥናቱም ያተኩረውም በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚያስተምሩ መምህራንና ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ በእነዚህም ትምህርት ቤቶች ውስጥ 19 ምድቦች ይገኛሉ፡፡ አጠቃላይ የተማሪዎች ብዛት 901 ናቸው፡፡በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሶስት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ይገኛሉ፡፡

### 3.3. የተጠኚዎች ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት የትምህርት ቤት፣ የመምህራን ፣የምድብና የተማሪዎች ናሙና መረጣ ተካሄዷል፡፡ የእያንዳንዱ ናሙና አመራረጥም ቀጥሎ በሰንጠረዥ መልክ ቀርቧል፡፡

**ሰን.ጠረዥ .3 1. በጥናቱ የተካተቱ ትምህርት ቤቶች፣የምድቦች፣የተማሪዎች እና የመምህራን ብዛት  መጠን እና የምልከታ ጊዜ መግለጫ**

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት ምድብና ናሙና | | | | የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ብዛት | | የምልከታው ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የተማሪዎች ብዛት | የተማሪዎች ናሙና | የምድብ ብዛት | የምድብ ናሙና | በትምህርት ቤት | የመጠይቅ ናሙና | |
| 1 | ጉደያ ቢላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 401 | 30 | 9 | 1 | 1 | 1 | 2 |
| 2 | ጃሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 380 | 30 | 8 | 1 | 1 | 1 | 2 |
| 3 | ዜንጊ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 120 | 30 | 2 | 1 | 1 | 1 | 2 |
| ድምር | 3 | 901 | 90 | 19 | 3 | 3 | 3 | 6 |

### 3.3.1.የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ወለጋ ዞን በጉደያ ቢላ ወረዳ በሚገኙ ሦስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ ሲሆን ትምህርት ቤቶቹም በጠቅላይ የናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡የተመረጡት ትምህርት ቤቶችም ጉደያ ቢላ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ጀሬ 2ኛደረጃ ትምህርት ቤት እና ዘንጊ 2ኛደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው፡፡

### 3.3.2.የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን በጉደያ ቢላ ወረዳ በሚገኙ ሦስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ  ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ብዛት ሶስት ሲሆኑ የእነዚህም መምህራን ቁጥር ቢላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህር፤ጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲሁም

ዜንጊ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንድ የአማርኛ ቋንቋ መምህር ይገኛሉ፡፡እነዚህም መምህራን በጥቅል የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠው የጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል፡፡

**ሰንጠረዥ .3 .2. . የተተኳሪ መምህራን ዳራዊ መግለጫ**

| ተራ ቁ. ተ. | የትምህርት ቤት ስም | ጾታ | የትምህርት ደረጃ | የትምህርት መስክ | የማስተማር ልምድ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ጉደያ ቢላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ወ | ቢኤ | አማርኛ | 25 |
| 2. | ጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ሴ | ቢኤ | አማርኛ | 15 |
| 3. | ዘንጊ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | ወ | ቢኤ | አማርኛ | 11 |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው መረጃ እንዲሰጡ የተመረጡት መምህራን ከፆታ አንጻር አንድ ሴት እና ሁለት ወንዶች ናቸው፡፡ ከትምርት ደረጃ አንጻር ደግሞ ሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸውና በአማርኛ ትምህርት የሰለጠኑ ሲሆኑ ከ11 እስከ 25 ዓመታት ያህል ያገለገሉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ተፈላጊው መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

## 3.3.3.የምድብና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

### 3.3.3.1.የምድብ ናሙና አመራረጥ

ካሉት ምድቦች ዘጠነኛ ክፍል በአመቺ ናሙና ዘዴ ከተመረጠ በኋላ ተተኳሪ መምህራን ከሚገቡባቸው ምድቦች(ክፍሎች) ውስጥ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት አንድ አንድ ምድብ በድምሩ ሶስት ምድቦች በተራ የዕጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ የተመረጡ ሲሆን ምድቦቹም፡- 9A (ከዘንጊ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ፣ 9B (ከጉደያ ቢላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) እና 9D (ከጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ናቸው ፡፡

### 3.3.3.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ከላይ ከተጠቀሱት ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተመረጡት ሶስት ክፍሎች(ምድቦች) ውስጥ በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ውስጥ በአማካይ 62--65 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡የመነሻ ቁጥር ዕጣ ከተለየ በኋላ አንድ አልፎ አንድ በመውሰድ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ሰላሳ(30) በአጠቃላይ ዘጠና(90) ተማሪዎች በተራ የዕጣ ናሙና ዘዴ ተመርጠው የጽሁፍ መጠይቁን

እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ተማሪዎቹ የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታውን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ከተማሪዎቹ የሚሰበሰበው መረጃም በተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘውን መረጃ ያጠናክራል በሚል እሳቤ የተካሄደ ነው፡፡

## 3.4.የመረጃ መሰብስቢያ መሳሪያዎች

የዚህ ጥናት ትኩረት የዘጠነኛ ክፍል መምህራን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡የጥናቱ አካባቢ፣የትምህርት ቤቶቹ፣የመምህራን እና የተማሪዎቹ ናሙና ከተመረጡ በኋላ መረጃ የመሰብሰቡ ስራ ተከናውኗል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች አስተማማኝ ይሆኑ ዘንድም በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ መረጃዎች ለማሰባሰብ ጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 3.4.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ

በተጠኚ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተስተዋለው የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የመማር ማስተማር ክንውን ለመታዘብ በቼክሊስት የተደገፈ ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያነት በጥቅም ላይ የዋለ ዋነኛው መሳሪያ ነው፡፡ምልከታው በሦስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩትን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አካቷል፡፡ምልከታው ውስን(Fixed) የምልከታ ስልትን መሰረት ያደረገ ሲሆን በዚህ ውስን (Fixed) የምልከታ ስልት በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ከሚተገበሩ ክንውኖች ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎች በተዘጋጀው የመከታተያ ቅጽ(Check list) ላይ በመሙላት መከናወን ወይም አለመከናወኑን በማየት እነዲረጋገጥ ተደርጓል፡፡

የመከታተያ ቅጹም ቀደም ሲል በምእራፍ ሁለት ከተገለጸው ጽንሰ ሃሳብ በመነሳት የተዘጋጀ ነው፡፡ ምልከታው የተካሄደው በተጠኚ ትመምህርት ቤቶች በሚገኙ ሶስት የዘጠኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ በመታዘብ ነው፡፡ምልከታው በእያንዳንዱ ተጠኚ መምህራን ላይ ሁለት ሁለት ጊዜያት ተካሄዷል፡፡

### 3.4.2. የፅሑፍ መጠይቅ

የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማሰባሰብ እንዲቻል ለ90 (ዘጠና)ተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ቀርቧል፡፡የፅሑፍ መጠይቁ

መሰረታዊ አላማ በተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች የተገኘውን ውጤት ለማገናዘብ እና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ነው። ይህም የፅሑፍ መጠይቅ በአማካሪዬ ተገምግሞና አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎበት በስራ ላይ ውሏል።የፅሑፍ መጠይቁ በተቻለ መጠን ግልጽ ቋንቋን በመጠቀም የተዘጋጀ ሲሆን አጥኚዋ በየትምህርት ቤቶቹ በመገኘት በናሙናነት የተመረጡትን ተማሪዎች ለብቻቸው በመለየት ስለመጠይቁ አጠቃላይ ዓላማ እና አሞላል ማብራሪያ ከተሰጣቸው በኋላ በየግላቸው እንዲሞሉት ተደርጓል።

### 3.4.3. ቃለ መጠይቅ

ከጽሁፍ መጠይቅና ምልከታ በተጨማሪ ቃለ መጠይቅም የዚህ ጥናት አጋዥ የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያ በመሆን አገልግሏል። ቃለ መጠይቁ በጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ ለዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን አላማውም መምህራኑ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የንግግር ክሂልን እንዴት እንደሚያቀርቡ፣ ስለ ቋንቋው ንግግራዊ አቀራረብ ያላቸውን ግንዛቤ ለመረዳትና በአተገባበሩ ዙሪያ ስለሚያጋጥሙ ችግሮች መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ነው።ከዚህ በተጨማሪም ቃለ መጠይቁ የመምህራንን ዳራዊ መግለጫ የያዘ ሲሆን ለጥናቱ እንዲስማማ ሆኖ ከተዘጋጀ በኋላ በአማካሪዬ ተገምግሞና አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎበት በግልጋሎት  ላይ ውሏል።

## 3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ከመምህራን ቃለ መጠይቅ ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅና ከምልከታ ከተሰበሰቡት መረጃዎችና ውጤቶች በመነሳት በምዕራፍ አንድ ስር ለቀረቡት የዓላማ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ትንተና የተደረገበት ስልት ዓይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴዎች ሥራ ላይ ውለዋል። ትንተናው መረጃዎቹ በሚያነሱት ጉዳይ ተከፋፍሎ በሰንጠረዥ ውስጥ በቁጥር እና በመቶኛ ቀርቧል።ሌላው በመረጃ ትንተና የታየው ውጤት የሚብራራበት ነው።ውጤቱንም ከቀርቡት ይዘቶች እና ክንውኖች፤ በመማር ማስተማሩ ሂደት ከሚሰራበት ስነ-ዘዴ እና አተገባበር፤ በክለሳ ድርሳናት ቅኝት ስር ከሰፈሩት ንድፈ ሃሳቦች ጋር መጣጣማቸውን ለመፈተሽ መምህራን ያላቸውን ግንዛቤ እንዲሁም ከስነ-ዘዴው ውጤታማነት አንፃር ተብራርቶ ቀርቧል።

# ምዕራፍ  አራት

# የመረጃዎች  ትንተና

የዚህ ምዕራፍ ዓላማ  በ9ኛ ክፍል ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንግግር ክሂል አተገባበርን በመፈተሽ፣የትምህርት አቀራረባቸውን በተመለከተ ውጤታማ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን መመርመር ነው፡፡በመሆኑም በምዕራፍ ሦስት እንደተገለፀው የዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ  መሳሪያዎች  ምልከታ፣የጽሑፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ በእነዚህ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በዝርዝር እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 4.1. ከምልከታ ፣ ከጽሁፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች  ትንተና

### 4.1.1 መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ በአቀራረብ  ደረጃ  ምን ያህል እንደሚተገብሯቸው መፈተሽ

በንግግር ትምህርት አቀራራብ  ተማሪዎች ወደ ዋናው ተግባር ከመግባታቸው በፊት የትምህርቱን ዓላማ በመግለጽ  የማነቃቃት ስራ ታስቦ የሚከናወን ከሆነ ፣የተማሪዎችን ፍላጐት በማነሳሳት ተግባቦታዊ ችሎታቸውን የሚያሳድግ፣ከገጠመኞቻቸው፣ከእለት እለት ህይወታቸው ጋር አብረው የሚሄዱ ተግባራትን በመምረጥና እርሱን መሰረት በማድረግ ቀጣይ ሥራቸውን የሚያከናውኑበትን ሁኔታ በግልፅ ማዘጋጀት፣የተፈለገውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ አይነተኛ መሳሪያ መሆኑን የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ተማሪዎች የንግግር ተግባራቱን እንዴት ማቅረብ እንዳለባቸው ሞዴል  በመስጠትና  በነፃነት እንዲናገሩ  ማድረግ  የመምህሩ ዋና ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም ከርዕሱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መርጃ መሳሪያዎች ለምሳሌ የተለያዩ ሥእሎችን በመጠቀም የዕለቱን ትምህርት ዓላማ መንገር፣ ምን  ምን  ተግባራትን በቅደም ተከተል  እንደሚሰሩ ማሳወቅ፣ ስለሚያከናውኑት ተግባር ግልፅ መመሪያ መሰጠት፣ መመሪያውን መረዳታቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ለሚያከናውኑት ተግባር ተገቢነት ያለው አቀማመጥ መምረጥ የመምህሩ ዋና ተግባር  ነው ፡፡

ከዚህ መሰረተ ሀሳብ በመነሳት የተደራጀ ምልከታ ቅፅ በቅድሚያ በማዘጋጀት በክፍል ውስጥ ምልከታ ወቅት ተተኳሪ ነጥቦች መከናወን ወይም አለመከናወናቸውን መከታተል የተቻለ ሲሆን የእያንዳንዱ የንግግር ክሂል አቀራረብ ደረጃ ክንውን ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠየቅና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ ጋር እየተመሳከረ የመረጃው ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ.4.1. መምህሩ የዕለቱን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ተግባራትን አቀራረብ አስመልክቶ በምልከታ የተገኘን ውጤት የሚያሳይ መግለጫ**

| ተራ ቁ. | የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይ | |
| | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| 1 | የተወሰነ ግልፅ ዓላማ ለተማሪዎች ቀርቦ ነበር? | 3 | 50% | 3 | 50% |
| 2 | የትምህርቱ አቀራረብ የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መሰረት ያደረገ ነበር? | 6 | 100% | --- | --- |
| 3 | በትምህርቱ አቀራረብ የፈጠራ ስራ እና የማስተማሪያ መሳሪያ ቀርቦ ነበር? | --- | --- | 6 | 100% |
| 4 | የትምህርቱ ይዘት የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ ነበር? | 4 | 67% | 2 | 33% |
| 5 | የንግግር ትምህርቱን በበቂ ሁኔታ ይለማመዱ ዘንድ ተማሪዎችን የማነቃቃት ተግባር ተከናውኗል? | --- | --- | 6 | 100% |
| 6 | የቀረቡት መመሪያዎች ለተማሪዎቹ ግልፅ ነበሩ? | 4 | 67% | 2 | 33% |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ በተካሄዱት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ተከታታይ ምልከታዎች ውስጥ የተማሪዎችን ችሎታ ለማዳበር የተለያዩ የንግግር ተግባራትን ወደ ክፍል በማምጣት የዕለቱን ትምህርት ከማቅረባቸው በፊት አላማውን በመዘርዘር ያቀረቡት በቁጥር 3 (50%) ሲሆኑ፤ አላማውን ሳይገልፁ ወደ ዕለቱ ትምህርት የገቡ 3 (50%) ናቸው፡፡

እንደሚታወቀው የዕለቱ ትምህርት ከማቅረቡ በፊት ማንኛውም መምህር ስለሚያስተምረው ጉዳይ አላማውን በዝርዝር ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡፡በተጨማሪም ከተማሪዎቹ ዕድሜና ፍላጐት፣ ስነ ልቦና፣ ከትምህርት ደረጃ፣ ከተማሪዎቹ ማንነትና ይዘውት ከመጡት ባህል፣ ወግና ልማድ ጋር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበር ተማሪዎችን የሚያነሳሱና የሚያሳትፉ እንዲሁም ለውይይትና ክርክር የሚጋብዙ ርዕሶችን በቂ ጊዜ ወስዶ መምረጥ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡

ሆኖም ግን ከዚህ ምልከታ ለመረዳት እንደተሞከረው የተወሰኑት መ ም ህ ራ ን አላማውን ሲገልፁ፤ ሌሎች አልገለጹም፡፡ በመሆኑም ግልፅ አላማን በማስገኘት ረገድ ያተኮረ የንግግር ተግባር ልምምድ በማቅረብ ረገድ የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን ያሳያል፡ እንዲሁም የዕለቱ ትምህርት ርዕስ የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መሰረት የማድረጉ ሁኔታ 6(100%) የትምህርቱን መርሃ ትምህርት መከተላቸውን በአግባቡ ያሳየናል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ሁሉም ተተኳሪ መምህራን ዋናው የዕለቱ ትምህርት አቀራረባቸው በተለያዩ የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎች ላይ የተመሰረተ አልነበረም፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪዎች የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴና የህይወት ገጠመኝ ያላገናዘበ በመሆኑ ትምህርቱን ውጤታማ አያደርገውም፡፡

ይህንን ሀሣብ Brown & Yule (1983) የንግግር ተግባራትን ስናሰተምር ተማሪዎች ማህበራዊ ግንኙነታችውን እንዴት አድርገው እንደሚመሰርቱ እና በክፍል ውስጥ በምን መልኩ እንደሚተገብሩ ማስተማርና ከክፍል ውጪም ባለው ህይወታቸው ጠቃሚ መሆኑን ማስተማር፣ ይህም ሲሆን ከጓደኛቸውና ከቤተሰብ አባላት ጋር በውይይት መልክ እንዲተገብሩ ይረዳቸዋል በማለት ገልፀዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎች የንግግር ክሂልን ሲማሩ ከህይወት ገጠመኛቸው ጋር የተያያዘ ትምህርት ሊቀርብላቸው ይገባል፡፡

በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ተግባራት በምን ዓይነት ደረጃ እንደሚቀርቡ በማያሻማ ሁኔታ አውቆ የተማሪዎቹን ፍላጎትና ስሜት እንዲሁም የትምህርት ደረጃ ሊመጥኑ የሚችሉ የተለያዩ ሞዴሎችን በማምጣት ወደ ዋናው ሥራ የማስገባት ሁኔታ ከማንኛውም የቋንቋ መምህር የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡ በዚህም መሠረት 4(67%) ያቀረቡት ርዕሰ ጉዳይ

የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ የሚመጥን ሲሆን 2(33%) የተማሪዎችን የትምህርትና የዕድሜ ደረጃ ያገናዘበ ነው ለማለት አያስችልም፡፡ ለተማሪዎቹ ልምምድ የተሰጣቸው ርዕስ "ለሴትና ወንድ ልጆች የትዳር ጓደኛ ለመምረጥ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም" የሚል ሲሆን፤ ይህ ርዕስ ተማሪዎቹ ብዙ በማያውቁትና ባልሞከሩበት ተግባር ላይ የተመሰረተው ነው፤ የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ መሰረት አላደረገም ፤ሆኖም ግን ሌላው ርዕስ የቀረበው ተመመጣኝ በሆነ መልኩ በመሆኑ ትምህርቱ በዚህ ረገድ መልካም እንደነበር ያሳየናል፡፡

በሌላ በኩል በክፍል ምልከታው የተከናወነውን ተግባር ስንመለከት ተጠኚ መምህራን ተማሪዎች ወደ ዋናው ተግባር እንዲገቡ ለማነቃቃት ባለመሞከራቸው የተሠጣቸውን ሥራ ለመጀመር ብዙ ደቂቃዎችን ፈጅቶባቸዋል፡፡ ተግባሩ ይቀርብ የነበረው በክርክር መልክ በመሆኑ ወደ ክርክር ከመግባታቸው በፊት ማነቃቂያ ሳይሆን የክርክሩን ሂደት ነበር መምህሩ ሲገልፁ የነበረው፡፡በመሆኑም የክርክሩ ሂደት ሳቢና ማራኪ ባልሆነ መንገድ የቀረበ እና ተማሪዎች የእርስ በእርስ ያለመደማመጥ እና ሥርዓቱን ያልጠበቀ ክንውን እንዲሆን አድርጐታል፡፡

ይህ የሚያሣየን መምህራን የማነቃቃት ሥራ ባለመስራታቸው፣ ውይይትና ክርክር መድረክ ላይ እንዴት እንደሚያቀርቡ እና ምን ምን ነገሮች እንደሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ባለማቅረባቸው ተማሪዎቹ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው እንዳይናገሩ ሆነዋል፡፡የሚቀርቡት መመሪያዎች ግልጽነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህም ሲባል ለተማሪዎቹ በትምህርት የሚቀርበው መመሪያ በሚገባ ተብላልቶ ወደ ትምህርቱ ከመግባታቸው በፊት መምህራን ለተማሪዎቹ ግልጽና ሊተገብሩት በሚችሉበት ሁኔታ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም 4 (67%) ለተማሪዎች ግልፅ በሆነ መልኩ የቀረበ ሲሆን 2 (33%) የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃና እድሜ ያላገናዘበ በሆነ መልኩ ቀርቧል፡፡

ከፍ ሲል ባየነው ሠንጠረዥ እንደተጠቀሰው በክፍል ውስጥ በተደረጉ ተከታታይ ምልከታዎች የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት አብዛኛዎቹ መምህራን የዕለቱን የንግግር ትምህርት አቀራረብ በተመለከተ ምንም ዓይነት የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያ እንዲሁም ወደ ዕለቱ ትምህርት ከመግባታቸው በፊት የማነቃቂያ ተግባር ያላከናወኑ መሆናቸውን ለመረዳት

ተችሏል፤ይህም ከጽሑፍ መጠይቁና ከቃለ መጠይቁ ውጤት ጋር ተመሰሳነት አለው።

#### 4.1.1.1 የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ መግለጫ

ጥያቄ.ቁ.1.የንግግር ክሂል ትምህርት ከመቅረቡ በፊት ዓላማውን በግልጽ ያቀርባሉ?

ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መልስ እንደሚያመለክተው ተተኳሪዎቹ መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርት ከመቅረቡ በፊት አላማውን በግልጽ ያቀርባሉ? ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ 2(67%) መምህራን "ሁል ጊዜ" እናቀርባለን ሲሉ አንድ (33%) መምህርት ግን "አብዛኛውን ጊዜ" በማለት ገልፃለች። እንደሚታወቀው አንድ መምህር የመማር ማስተማሩን ክንውን ለመተግበር ዓላማ ሊኖረው ይገባል። እንደ በድሉ ዋቅጅራ (2007) የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ የማስተምር ዋና አላማው ተማሪዎች ሀሳባቸውን ያለምንምችግር እንዲገልፁ በራስ የመተማመን፤ሀሳብን በምክንያትና ዉጤት አቀናጅቶ ማቅረብ፤ የቋንቋን ስርዓት ጠብቀው እንዲናገሩ ያስችላቸዋል በማለት ገልፀዋል።ስለዚህ ከምልከታው የተገኘው መረጃ እንደተረዳነው ከቃለ መጠይቁና ከጽሁፍ መጠይቁ ጋር ተመሳሳይነት አለው።

ጥያቄ ቁ.2. የንግግር ክሂል ተግባር በክፍል ውስጥ ከመቅረቡ በፊት በተለያዩ መንገዶች ተማሪዎችን ያነቃቃሉ?

መምህራን ወደ ዋናው የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባር ከመግባታቸው በፊት የማነቃቃት ሥራ ማከናወናቸውና አለማከናወናቸው ተጠይቀው ሲመልሱ አንድ(33%) መምህርት "ሁል ጊዜ"አከናውናለሁ ሲሉ ሁለት(67%)ቱ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚተገበሩ ገልፀዋል ። ነገር ግን ከጽሁፍ መጠይቁና ከምልከታው መረጃ ጋር ሲነፃፀር ሁሉም መምህራኖች የማነቃቂያ ተግባር እንዳላከናወኑ ለመረዳት ተችሏል።

ጥያቄ ቁ.3. ከንግግር ክሂል ትምህርት በፊት ስለ ንግግር አቀራረብ ተማሪዎች እንዲያውቁ ያደርጋሉ?

ከንግግር ክሂል ትምህርት በፊት ስለ ንግግር አቀራረብ ተማሪዎች እንዲያውቁ ያደርጋሉ? ተብለው ሲጠየቁ አንድ(33%) መምህር "ሁል ጊዜ" ለክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አቀራረብን አሳውቃለሁ ሲሉ ሁለት(67%)ቱ ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" አንደሚተገብሩት ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም ተማሪዎችን ከንግግር ክሂል ትምህርት በፊት ስለ ንግግር ክሂል

አቀራረብ የማሳወቁ ሁኔታ በመምህራን በኩል ደካማ መሆኑን ያመላክተናል፡፡

ጥያቄ ቁ.4.ለንግግር ክሂል ትምህርት የሚሆኑ አጋዥ መርጃ መሳሪያዎችን በማምጣት ያስተምራሉ ?

*ለንግግር ክሂል ትምህርት የሚሆኑ አጋዥ መርጃ መሳሪያዎችን ከመጽሐፉ ጥያቄ ውጪ በማምጣት አቀርባለሁ ያሉ ተተኳሪ መምህር አንድ(33%) "ሁልጊዜ"አቀርባለሁ ሲሉ፣ ሁለት(67%) መምህራን ደግሞ "ጨርሶ" አላቀርብም በማለት መልሰዋል፡፡ ይህ የሚ ያሳየን የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበር በቂ ጊዜ ወስዶ የሚያነቃቁ፤የማ ያሳትፉና ለውይይት የሚጋብዙ ርዕስ ጉዳዩችን በመምረጥ ረገድ መምህራኑ ያላቸው ተነሳሽነት ከአንድ መምህር በስተቀር ሌሎቹ ደካማ መሆናቸውን ያሳያል ፡፡*

ጥያቄ.ቁ 5.ተማሪዎቹ በቀረበላቸው ተግባር መሰረት የማስመሰልና የመደጋገም ስራዎችን እንዲያከናውኑ ያደርጋሉ?

በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ተማሪዎችን በማነቃቃት የተለያዩ ሞዴል ተግባራትን በመስጠት አጋዥ መርጃ መሳሪያዎችን ተጠቅሞ የማስመሰልና የመደጋገም ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማድረግ ጠቀሜታው ላቅ ያለ መሆኑን በተለያዩ ምሁራን በክለሳ ድርሳናት ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ሀሳብ በመነሳት ተማሪዎቹ በቀረበላቸው ተግባር መሰረት የማስመልና የመደጋገም ስራዎችን እንዲያከናውኑ ያደርጋሉ?ተብለው ሲጠየቁ ሁሉም(100%)መምህራን ተግባሩን "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚያከናውኑ ገልፀዋል፡፡ ከምልከታው ጋርም ይህ ተግባር ተመሳሳይ መውጤት ታይቶበታል፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው በንግግር ክሂል አቀራረብ ወቅት መምህራን ከመጽሐፉ ከቀረቡት የመለማመጃ ጥያቄዎች ውጪ የተለያዩ የመርጃ መሳሪያዎች በማቅረብ የመማር ማስተማርን ተግባር እንደማያከናውኑ ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ .4.2. የንግግር ክሂል ተግባራት አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎች ምላሽ መግለጫ

| ተ. ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን ያቅተኛል | | አልስማም | | በፍፅም አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ % | በቁጥር | በመቶኛ % | በቁጥር | በመቶኛ % | በቁጥር | በመቶኛ% | በቁጥር | በመቶኛ% |
| 1 | የንግግር ትምህርት ክሂልን ተግባር ከማከናወናቸው በፊት አላማው ይገለፅላችኋል | 30 | 33.3 | 35 | 38.9 | 12 | 13.3 | 7 | 7.8 | 6 | 6.7 |
| 2 | የንግግር ክሂል ተግባር በክፍል ውስጥ ከመቅረቡ በፊት በተለያዩ መንገዶች ያነቃቃሉ | 20 | 22.2 | 28 | 31.1 | 18 | 20 | 16 | 17.8 | 8 | 8.9 |
| 3 | የንግግር ክሂል ተግባራት ከመጀመራቸው በፊት አጭርና ግልፅ መመሪያ ይሰጡ ነበር | 23 | 25.6 | 34 | 37.7 | 20 | 22.2 | 8 | 8.9 | 5 | 5.6 |
| 4 | ዋናውን የመናገር ተግባር ተማሪዎች ከማከናወናቸው በፊተ ሞዴል (ምሳሌ የሚሆኑ) ተግባሮች ይቀርቡ ነበር | 23 | 25.6 | 32 | 35.6 | 20 | 22.2 | 8 | 8.9 | 7 | 7.7 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚታየው የንግግር ክሂል ትምህርት ከመከናወኑ በፊት ዓለማው ተገልፆላቸው እንደነበር ተጠይቀው 30(33.3%) ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ በማለት ሲመልሱ፣ 35(38.9%) እስማማለሁ ፣12(13.3%) ተማሪዎች ለመወሰን ያቅተኛል፣

7(7.8)አልስማም ፣6(6.7) ተማሪዎች በፍፅም አልስማማም በማለት መልስ ሰጥተዋል። በመሆኑም ከተወሰኑ ተማሪዎች ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው የዕለቱ ትምህርት ከመቅረቡ በፊት የትምህርቱ ዓላማ እንደሚገለፅላቸው አዎንታዊ መልስ መስጠታቸውን መረጃው ያሳየናል።በተደረገው ተከታታይ ምልከታ መረጃ መሰረትም አንድ መምህር ዓለማውን ያለመግለጹን መረጃው የሳያል።

እንዲሁም ተማሪዎች ከሞሉት መጠይቅ ውስጥ መረዳት እንደተቻለው የንግግር ክሂል ተግባራት ከመቅረቡ በፊት በተለያዩ መንገዶች የማነቃቃቱ ሁኔታ ይተገበራል ወይ? ተብለው ሲጠየቁ 22.2% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 31.1% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 20% ተማሪዎች ለመወሰን ያቅተኛል፣ 17.8% ተማሪዎች አልስማማም፣ 8.9% ተማሪዎች ደግሞ በፍፁም አልስማማም በማለት ገልፀዋል። ስለዚህ ከተማሪዎቹ መልስ መረዳት የሚቻለው የዕለቱ ትምህርት ከመቅረቡ በፊት መምህራን ተከታታይነት ባለው መንገድ የተማሪዎች የቀደመ ዕውቀት ከዕለቱ ትምህርት ጋር ለማዛመድ፣ የዕለቱ ትምህርት በምን ዙሪያ እንደሚያጠነጥን ፍንጭ ለመስጠት፣ የተማሪዎችን ትኩረት ወደ ዕለቱ ትምህርት ለመሳብ የሚያደርጉት ጥረት አዎንታዊ መሆኑን መረጃው ያሳየናል።

የመምህራን የቅድመ ንግግር ክሂል ተግባር ክንውን በሚመለከት ለተማሪዎች የቀረበው ጥያቄ የመምህራን የመመሪያ አስጣጥ የሚመለከት ነው። ለዚህም ጥያቄ 25.6% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 37.7% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 22.2% ተማሪዎች ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 8.9% ተማሪዎች አልስማማም፣ 5.6% ተማሪዎች ደግሞ በፍፁም አልስማማም በማለት መልሰዋል። Ur (1996.)የመምህራን ወደ ዕለቱ ትምህርት ከመግባታቸው በፊት መመሪያ የመስጠት ጠቀሜታ በሚመለከት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስለሚያከናውኑት ተግባር ግልፅና እጥር ምጥን ያለ መመሪያ መስጠት የተማሪዎች ግራ የመጋባት ችግር ተቀርፎ ክንውኑ በተሳካ ሁኔታ እንዲሄድ ይረዳል" ይላሉ ከዚህ አኳያ ሲታይ የመምህራኑ ግንዛቤና አፈፃፀም በተማሪዎች እይታ በመካከለኛ ደረጃ ላይ ነው። በተከታታይ የተደረገው የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ እንደሚያሳየው ሁሉም ተተኳሪ መምህራን ይህንን ተግባር ሲያከናውኑ አልተመለከቱም። ተማሪዎች ወደ ዋናው የንግግር ተግባር ከመግባታቸው በፊት ሞዴል (ምሳሌ) የሚሆኑ ተግባሮች ይቀርቡ እንደነበር ተጠይቀው ሲመልሱ 25.6% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ 35.6% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 22.2% ተማሪዎች ለመወሰን ያቅተኛል፣ 8.9% ተማሪዎች አልስማማም፣ 7.7% ደግሞ በፍፁም አልስማማም

በማለት መልስ ሰተዋል፡፡

ይህንን በተመለከተ Harmer.(2007) የንግግር ክሂል ትምህርቱ ከመከናወኑ በፊት ስዕሎችን በማቅረብ ልዩነታቸውን መግለፅ እንዲችሉ ማድረግ፣ በሰንጠረዥ መልክ የቀረቡ መረጃዎችን ማሟላት እንዲችሉ ማድረግና የመሳሰሉት ሞዴሎች ቢቀርብላቸው ተግባራቱ የውስብስብነት ባህሪይ እንዳይኖራቸው ያደርጋል በማለት ጠቅሰዋል፡፡በዚህም መሰረት ጥቂት ተማሪዎች መምህራን ይህንን ተግባር ያከናውናሉ ብለው በተሰጣቸው መጠይቅ ቢያመላክቱም በተደረገው ተከታታይ ምልከታና ቃለ መጠይቅ መረጃ መሰረት አንድም መምህር ይህንን ተግበር ሲተገብር አልተስተዋለም፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ በአቀራረብ ደረጃ ከምልከታ፣ ከጽሁፍ መጠይቅና ከቃለ መጠይቁ ምላሽ ለመረዳት እንደተቻለው ወደ ዋናው ትምህርት ከመግባታቸው በፊት የማነቃቂያ ተግባር ሁሉም መምህራን ያለማከናወናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የእለቱን ትምህርት አላማ ከመግለጽ አንጻር የተወሰኑ መመህራን ብቻ ሲያቀርቡ ተስተውሏል፡፡

### 4.1.2 . መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርት ሲተገብሩ የልምምዱን ሂደት መመርመር

**ሰንጠረዥ- 4.3 .የንግግር ክሂል ትምህርት የልምምድ ተግባርን የሚያሳይ ከምልከታ የተገኘ መግለጫ**

| ተ/ቁ | የማስተማር ዘዴው ትግበራ | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ(%) | በቁጥር | በመቶኛ(% |
| 7 | በልምምድ ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ጐልቶ ይታይ ነበር? | 3 | 50% | 3 | 50% |
| 8 | ተግባሩን ለማለማመድ የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ ተጠቅመዋል? | 3 | 50% | 3 | 50% |
| 9 | የንግግር ክሂልን ማለማመድ የሚያስችሉ ተግባራትን (ክርክር፣ በጭውውትና በውይይት መልክ) ተከናውኗል? | 4 | 67% | 2 | 33.3% |
| 10 | የንግግር ክሂል ልምምዱን ለማድረግ በግል፣ በጥንድ ወይም በቡድን የማስተማር ስነ-ዘዴ ተጠቅመው ነበር? | 6 | 100% | __ | __ |

እንደ Byrne (1986) አገላለጽበ ልምምድ ወቅት የሚቀርቡ ይዘቶች ተማሪዎች በተሠጣቸው ሞዴል መሰረት ተለማምደው ቀጣዩን የንግግር ትምህርት ልምምዶች እንዲፈፅሙ አቀራረቡ ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር አብሮ የሚሔድ፣ ጊዜ የማይወስድ፣ አጭርና ግልጽ እንዲሁም ከተማሪዎች ነባራዊ ህይወት ጋር ተመሳሳይ መሆን ይኖርበታል ይላሉ፡፡ ነገር ግን የምልከታው መረጃ እንደሚጠቁመን 50%ቱ የቀረበውን የንግግር ክሂል ትምህርት ገለጻ ሲሰጡ የቀሩት 50%ቱ ግን ሳይሰጡ ወደ ልምምድ እንዲገቡ በማድረጋቸው ተማሪዎች የሚሰሩትን ስራ በአግባቡ ሳይረዱ በቀጥታ ወደ ልምምድ ተግባር የገቡበት ሁኔታ ታይቷል፡፡ ይህ በመሆኑ የተወሰኑት ተማሪዎች ተሳትፏቸው በከፊል እንደነበር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

መምህራኑ በትምህርት የተመደበውን ጊዜ ለማነቃቂያ ፣ ለማስተዋወቂያ ፣ ለማለማመጃ ለማጠናከሪያና ለመገምገሚያ ወይም ማጠቃለያ ከፋፍለው በዕለቱ ትምህርታቸው አሰጣጥ ላይ አልተስተዋለም፡፡በሰንጠረዥ ላይ እንደተገለጸው ወደ ትምህርቱ ከመግባታቸው በፊት የማነቃቂያ ጊዜ ሁሉም መምህራን አለመስጠታቸው ተገልጿል፡፡ በመሆኑም በምልከታው እንደተስተዋለው ጊዜን በአግባብ ከፋፍሎ የመጠቀሙ ሁኔታ ሳይሆን በጥቅል ተግባሩ ሲከናወን ታይቷል፡፡

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ ማስተዋል የሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራኖች ልምምዱን ለማድረግ የተጠቀሙት በክርክርና በውይይት መልክ 4(67%) ሲሆን 2(33%) የመማር ማስተማር ተራክቦ በግል ነው፡፡ ልምምዱንም ለማከናወን የተመረጡት ርዕሶች *"የጫት መቃም ሱስ ማቆም ይቻላል ወይስ አይቻልም?" እና "የትዳር ጓደኛ ለመምረጥ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም?" የሚሉት ነበሩ፡፡* በክርክር ልምምዱ ወቅት በምልከታ እንደታየው መምህሯ ለተማሪዎቹ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ገለጻ ከሰጡ በኋላ ተማሪዎች ቦታቸውን ያዙ፤በመቀጠልም ድምፃቸው በማይሰማ ሁኔታ ዳኞች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለተማሪዎች ከገለፁ በኋላ የክርክር ልምምዱ ቀጠለ፣ በዚህን ወቅት የክፍሉ ተማሪዎች ይረብሹ ስለነበር ተከራካሪዎቹ ምን እንደሚሉ በግልፅ አይሰማም ነበር፡፡

ሌላው በውይይት መልክ የቀረበው ልምምድ ነው፡: እንደ Tericia (1996) አገላለፅ ውይይት ተማሪዎች ለምልልስ አስፈላጊ የሆነ ቋንቋ እንዲጠቀሙ ያበረታታል፡፡ በሌላኛው ተናጋሪ ላይ

በተወሰነ ጊዜ ምስል እንዲኖረው ያደርጋል። በርግጥም ውይይት ከሌሎቹ ተግባራት የበላይነትን ይይዛል። ይህም ለተማሪዎች የእርስ በእርስ ግንኙነት አጋጣሚ ይፈጥራል በማለት ያስቀምጣሉ።ከምልከታው እንደተረዳነው አብዛኛው መምህራን የንግግር ልምምድ ተግባሩን ያከናወኑት 67% በክርክር፣ በውይይት እና በጭውውት ሲሆን፤ 33% በተናጠል ትግበራ እንደነበር ያመለክታል።

Tricia (1996) መምህራን ሚናን ከተለያዩ ተግባራት ማለትም ከቀላል ምልልስ እስከ ውስብስብ ውክልና ከተለያዩ ደረጃዎች ጋር በማያያዝ መተግበር ይችላሉ። የሚና ተግባር በእውነተኛ ህይወት ላይ የተመሰረተና ለነፃ ውይይት ቀላል ሆኖ ያገኙታል። ምክንያቱም ተማሪዎች ሌላውን ሰው መስለው ሲጫወቱ ይደሰታሉ። ግልፅ ግብ ያለው ሚና መጫወት ለነፃ ውይይት ዓላማና አቅጣጫ ያሳያል። የሚና ጨዋታ ውድድርና መተጋገዝን ያካትታል። ይህም ባህሪው ሳቢ ያደርገዋል በማለት ይገልፃሉ።በመሆኑም መምህራን የንግግር ልምምዱን ተግባር በዚህ መልክ ማከናወን ይኖርባቸዋል።ከምልከታው ማየት እንደተቻለው ሁሉም መምህራን በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን አከናውነውታል። በመሆኑም ማለት ይቻላል።

ሠንጠረዥ 4.4. የንግግር ክሂል ትምህርት የልምምዱን ተግባር የሚያሳይ ከመከታተያ የተገኘ መግለጫ

| | | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ(%) | በቁጥር | በመቶኛ(%) |
| 11 | በልምምድ ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሣተፉ ይደረግ ነበር? | 2 | 33% | 4 | 67% |
| 12 | ለንግግር የማይደፍሩ ተማሪዎች እንዲለማመዱ ይበረታቱ ነበር? | - | - | 6 | 100% |
| 13 | ልምምድ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዙ የተለያዩ ዘዴዎች ይጠቀሙ ነበር? | 2 | 33% | 4 | 67% |
| 14 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎች እርስ በርስ በመወያየት ልምምድ እንዲያደርጉ ይበረታቱ ነበር? | 4 | 67% | 2 | 33% |
| 15 | ተማሪዎቹ ያልገባቸውን ጥያቄዎች እንዲያቀርቡ ሰፋ ያለ ዕድል ተሰቷቸዋል? | - | - | 6 | 100% |
| 16 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎች ሲሳሳቱ ለመርዳት ጥረት ተደርጎ ነበር? | - | - | 6 | 100% |

Harmer( 2007) የንግግር ክሂልን ለማሳደግ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ሊያሳትፉ የሚችሉ ተግባራት መቅረጽ ያስፈልጋል፡፡ የንግግር ክሂል ተግባራት ሲዘጋጅ ተማሪዎቹ ሙሉ በሙሉ በትምህርቱ እንዲሣተፉ እድል የሚሰጡና ከልምምዱ በኃላ የመምህሩ ምጋቤ ምላሽ ግምት ውስጥ የሚያስገቡ ከሆነ ተማሪዎቹ በትምህርቱ እርካታ ያገኛሉ፡፡ ይህም ተማሪዎቹ የታለመውን አላማ በቀላሉ እንዲደርሱበት ይረዳል፡፡ ተግባራቱ ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፍ ከሆነ ክፍሉ ያለምንም ችግር ተግባቦቱ የሰመረ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎቹን በራስ የመተማመን ስሜት ከፍ በማድረግ በንግግር ሀሳብን መግለጽ የቋንቋ ትምህርት ክፍል ባህል እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፆኦ ያደርጋል በማለት ገልፀዋል፡፡በዚህም መሠረት በክፍል ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ የማድረጉ ፋንታ መምህሩ ለልምምዱ ይዞት የሚቀርበው የመለማመጃ ርዕስ ከፍተኛውን ሚና ይጫወታል፡፡ ከሠንጠረዡ ለመረዳት እንደተቻለው አንድ መምህር ብቻ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ጥረት ሲያደርግ

ታይቷል፡፡

ሁለቱ መምህራን ልምምዱን ሲተገብሩ የነበረው በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ መሆኑን ለመረዳት ተሞክሯል፡፡ በምልከታውም የታየው የተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ መድረኩን ይዘው ልምምዱን ሲያከናውኑ ተስተውሏል፡፡ ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን የማበረታታቱ ጉዳይ በሁሉም መምህራን ዘንድ አልታየም፡፡ ይህም በመሆኑ የንግግር ልምምዱ ተግባር ይከናወን የነበረ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡ Ur(1996) በልምምድ ወቅት ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች የመናገር ችግር ከሚያጋጥማቸው መካከል ዋና ዋናዎቹ መታቀብ፣ የሚናገሩትን ነገር ማጣትና ዝቅተኛ ወይም ሁሉን ያላማከለ ተሳትፎ ማድረግ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

በዚህም መሠረት ከምልከታው እንደተረዳነው 100% መምህራን እነዚህን ተማሪዎች መርዳት እንዳልቻሉና የመማር ማስተማሩን ተግባር በአግባቡ እንዳልተገበሩ ያመላክተናል፡፡ የትምህርቱ ተግባር ሲከናወን በተማሪዎች ዘንድ የተመጣጠነ ተሳትፎ ወይም ልምምድ መከናወን እንዳለበት እርግጥ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ Byrne(1987)ሲገልፁ፤ *"በክፍል ውስጥ በሚደረገው የንግግር ትምህርት ተግባራት ተሳትፎ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዝ መምህራን ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል"* ይላሉ፡፡

ከምልከታው እንደተመለከትነው አንድ መመህር ብቻ በልምምድ ወቅት ሁለት ተማሪዎች እየተፈራረቁ ሀሳባቸውን ሲገልፁ "እረ እባካችሁ! ተናገሩ ሀሳባችሁን በፈለጋችሁት መንገድ አቅርቡ፤አትፍሩ፤ሁለት ልጅ ብቻ የማስተምር መሰለኝ" በማለት ሀሳባቸውን ሲያቀርቡ ተስተውሏል፡፡ የተቀሩት መምህራን ባቀረቡት ሀሳብ ብቻ ክፍለ ጊዜው ተጠናቋል፡፡ እንዲያውም አንዷ መምህርት የክርክሩን ልምምድ ማጠቃለያ ሳይሰጡበት እና ምንም ሀሳብ ሳይናገሩ ተማሪዎቹ ብቻ ተለማምደው ክፍለ ጊዜው ተጠናቋል፡፡ ከዚህ መረዳት የምንችለው መምህራን ተግባሩን በአጥጋቢ ሁኔታ እንዳላከናወኑት እንመለከታለን፡፡

Harmer(2007) የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ማለማመድ የሚችሉ ተግባራትን ሲገልጹ ተማሪዎቹ የሚፈልጉትን ርዕስ በመምረጥ እርስ በርስ ቃለ መጠይቅ እንዲያደርጉ ማድረግ፤የተለያዩ መረጃዎችን ሰብስበው በማደራጀትና በመለማመድ በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ማድረግ ወይም በቤታቸው ያነበቡትን ቅንጫቢ ወይም ሙሉ ሥራ በንግግር እንዲያቀርቡ

ማድረግ፤በቡድን በመመደብ ከሚደግፉት ሀሣብ አንፃር ወግነው እንዲከራከሩ ማድረግ የተማሪዎቹን የንግግር ክሂል ለማዳበር ጥሩ መንገድ ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

በዚህ መሠረት ተማሪዎቹ በቡድን በመሆን እርስ በእርስ ውይይት ማድረግን በተመለከተ ከምልከታው መረዳት እንደተቻለው ሁለቱ መምህራን የንግግር ክሂል ልምምድ ተግባሩን ያከናወኑ ሲሆን አንድ መምህር ብቻ አለማከናወኑን ተመልክተናል፡፡ ለተማሪዎቹ የቀረበው ርዕስ ጉዳይ ግልጽ መሆንና የእነርሱን ደረጃ የመጠነ መሆን እንዳለበት እሙን ነው፡፡ በመሆኑም ከምልከታው ለመገንዘብ እንደተቻለው ተማሪዎቹ የተለያዩ ሀሳቦችን በመሰንዘር ሀሳባቸውን ሲያብራሩ የልምምዱ ተግባር ይከናወን የነበረው በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ ነበር፡፡ በዚህም ወቅት ሁሉም መምህራን ወይም 100% ለተማሪዎቹ ምንም ዓይነት የጥያቄ ዕድል ያልሰጡ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ Byrne(1987:74) መምህሩ በተማሪዎች ልምምድ ወቅት ሀሣባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ ማድረግ አለበት፡፡ ልምምዱንም ሲቆጣጠር እንደ ተማሪዎቹ ፍላጎት፤ እንደሚጠየቁት ጥያቄ ሁኔታ የተለያዩ እርዳታዎችን የሚያደርግና ምክር የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል፡፡ አብዛኛውን ተግባር መምህራን በጥሩ ሁኔታ ለተማሪዎች ካቀረቡና ተማሪዎችን ካለማመዱ መጨረሻ ላይ ተማሪዎቹ ምን ያህል መሻሻል እንዳሳዩ የሚመለከቱበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎች የራሳቸውን የቃላትና የሰዋሰው እውቀትን በመጠቀም ሀሳብ አፍልቀው የሚገልፁበት መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል በማለት ይገልፃሉ፡፡ስለዚህ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በልምምድ ወቅት መደገፍና ሲሳሳቱ ማስተካከል ይኖርባቸዋል፡፡ ምልከታው የተረዳነው ሁሉም መምህራን ተማሪዎቻቸው ሲሳሳቱ ዝም ብለው ሀሳባቸውን ከማዳመጥ በስተቀር ለማስተካከል የሞከሩ አልነበሩም፡፡ ስለዚህም የልምምዱ ተግባር በአግባቡ አለመከናወኑን ያመለክተናል፡፡

### 4.1.2.1.ተማሪዎች የንግግር ክሂል ተግባራትን እንዲለማመዱ ከማድረግ አንጻር ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ መግለጫ

ጥያቄ.ቁ.6. በክፍል ዉስጥ ለንግግር ክሂል ትምህርት የሚሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች በተማሪዎች የህይወት ገጠመኝ ዙሪያ እንዲለማመዱ ያደርጋሉ?

ከመምህራን ቃለ መጠይቅ እንደተመለከትነው በመማር ማስተማሩ ሂደት የመምህሩ ሚና ተማሪዎቹ ተግባራቱን ከራሳቸው የህይወት ገጠመኝ ዙሪያና ከአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ ተነስተው ሀሳብ የሚያቀርቡበትን መንገድ ተጠይቀው አንድ(33%) መምህርት "ሁልጊዜ" ሁለት (67%) መምህራን "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚያመቻቹ መልስ ሰጥተዋል፡፡ እንደሚታወቀው ማንኛውም ተማሪ ሀሳቡን በአግባቡ ለመግለፅ የሚችለው ከሚያዉቀውና ከገጠመኙ በመነሳትና ከህይወት ልምዱ ጋር በማዛመድ መሆኑ ግልፅ ነዉ፡፡ ከቃለ መጠይቁ ምላሽ እንደተረዳነው ሁለት መምህራን ይህንን ዕድል ሁል ጊዜ እንደማይሰጡ ሲገልፁ አንድ መምህርት ብቻ ይህንን ተግባር እንደምታከናውን ገልፃለች፡፡

እንደ Harmer(1995) በተግባር ሂደት ተማሪዎች አስቀድመው በተወሰነ ነገር ላይ ተዘጋጅተው ወይም ተለማምደው ተግባሩን እንዲያከናውኑት ማድረግ ጥቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ርዕሱን ተማሪዎች እራሳቸው መምረጥ የሚችሉበትን ሆኔታ በማመቻቸት ሀሳባቸውን በክርክር ወይም በዉይይት መልክ እንዲያከናውኑ ማድረግ ይቻላል በማለት ገልፀዋል፡፡

ጥያቄቁ. 7.ተማሪዎች በራሳቸው የቋንቋ እውቀት ተጠቅመው በመለማመድ ሀሳባቸውን በነጻነት የሚገልፁበትን መንገድ ያመቻቻሉ?

ለጥያቄ ሰባት የቀረበው የመምህራን ምላሽ እንደሚያመለክተው የንግግር ክሂል ማለማመዱ ተማሪዎች በራሳቸው እውቀት ተጠቅመው ሀሳባቸውን በነፃ እንዲገልፁ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ተጠይቀው አንድ (33%) መምህር "ሁልጊዜ"እንደሚያመቻቹ ሲገልጹ ሁለት(67%) መምህራን "አንዳንድ ጊዜ" የልምምዱን ሁኔታ እንደሚያመቻቹ መልስ ሰጥተዋል፡፡ተማሪዎቹ በቋንቋቸው ተጠቅመው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳባቸዉን በነፃ መግለፅ የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት፣ የፍራሀትን ስሜት

እንደሚቀንስ ከማድረጉም በላይ በራሳቸው እንዲተማመኑ ያደርጋቸዋል በማለት Harmer (1995) ይገልፃሉ፡፡

ጥያቄ ቁ.8. አብዛኛውን ጊዜ ለመናገር የማይደፍሩና ሀሳባቸውን ለመግልፅ የሚያዳግታቸውን ተማሪዎች እንዲናገሩ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ያበረታታሉ?

ከላይ የቀረበውን ጥያቄ ከመለሱት ተተኳሪ መምህራን መካከል ሁለት (67%) መምህራን "አብዛኛውን ጊዜ" አንድ መምህር(33%) "አንዳንድ ጊዜ" ለመናገር የማይደፍሩና ሀሳባቸውን ለመግለፅ የሚቸገሩ ተማሪዎች በነፃነት እንዲናገሩ የተለያዩ መንገዶች እንደሚያመቻቹ ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ግን ከመምህራን ምላሽ እንደተረዳነው አንድም መምህር ይህንን ተግባር "ሁልጊዜ" እንዳላከናወኑ መምህራኑ ከሰጡት የቃለ መጠይቅ ምላሽ ለመረዳት ተችሏል ፡፡ ይህም ከምልከታው ውጤት ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

አብዛኞቹ ምሁራን የሚስማሙት በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት ብዙ ተማሪዎች በሚኖሩበት ክፍል ውስጥ በግል ከሚደረገዉ የመማር ማስተማር ሂደት በጥንቃቄ የሚደረግ የቡድን ስራ በበለጠ መልኩ በክፍል ውስጥ ለመናገር የማይደፍሩትን ተማሪዎች የሚያበረታታ ሀሳባቸውን ለመግለፅ ቃላት የሚያጥራቸውን እንዲናገሩ የሚያነሳሳና አብዛኛውን ተማሪ በእኩል ሊያሳትፍ የሚችል በመሆኑ ተመራጭ ነው፡፡ በመሆኑም በልምምድ ተግባር ሂደት ወቅት መምህራኑ ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ተግባራዊ ማድረግ እንደሚኖርባቸዉ እንረዳለን፡፡

ጥያቄ ቁ.9. የንግግር ክሂል ትምህርትን ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ያስተምራሉ?

እንደ Beygete,.(1987) በአራቱ የክሂል ዘርፎች መካከል ጥብቅ ግንኙነት አለ የምንልበት ምክንያት አንዱን ክሂል በምናስተምርበት ጊዜ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ሁሉንም ክሂሎች ለማስተማር ስለምንገደድ ነው፡፡ እንዲሁም የንግግር ክሂል ከሌሎች ክሂሎች ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ቢኖረውም የራሱ የሆነ መለያ ባህሪ አለዉ፡፡ በተጨማሪም

የመናገርና ማዳመጥ ክሂል የማይነጣጠሉና አንደኛው ክሂል ከሌላኛው ክሂል ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ናቸው። ጥሩ ለመናገር ጥሩ አድማጭ መሆን እንደሚገባ በርካታ ምሁራን ይገልፃሉ። በመሆኑም የንግግርን ክሂል ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማስተማርን መምህራን ምን ያህል ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ተጠይቀዉ፤ አንድ(33%) መምህር "ሁል ጊዜ" ሁለቱ (67%) መምህራን "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚተገብሩት ከሰጡት ምላሽ መረዳት ተችሏል።

ጥያቄ. ቁ.10. ለተማሪዎች የንግግር ክሂልን ለማዳበር የሚታዩ ነገሮችን ማለትም፡-ስዕል፣ ቅርፃቅርፅ፣ ካርታዎች፣ ወዘተ.. በመስጠት እንዲለማመዱና እንዲናገሩ ያደርጋሉ?

የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚታዩ ነገሮችን ስዕል፣ቅርፃቅርፅ፣ካርታዎች ወዘተ..በመስጠት እንዲለማመዱ የማድረጉን ሁኔታ ተጠይቀው አንድ(33%) መምህር "ሁልጊዜ" በማቅረብ እንደሚጠቀሙና ሁለት(67%)መምህራን ደግሞ "አንዳንድጊዜ" እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል።ሆኖም ግን በተደረገው ተከታታይ የክፍል ወስጥ ምልከታ መረጃ መረዳት እንደተቻለው ይህንን ተግባር አንድም መምህር ተግባራዊ ሲያደርገው አልታየም ።

እንደ Harmer(2007) የንግግር ክሂል ተግባርን ግልፅ አድርጎ ለማስተማር የስዕሎችን ልዩነት እንዲገልፁ ማድረግ፤ አቅጣጫን ማሳየት በሰንጠረዥ መልክ የቀረቡ መረጃዎችን ማሟላት እንዲችሉ ማድረግ ተግባራቱ ቀላል ባህሪ እንዲኖረው ያደርጋል ይላሉ።

ጥያቄ. ቁ.11. ተማሪዎችን በጥንድና በቡድን በመከፋፈል ሀሳብ ለሀሳብ እንዲለዋወጡ ያደርጋሉ?

የተማሪዎቹን የንግግር ክሂል ለማዳበር ተማሪዎችን በጥንድና በቡድን በመከፋፈል ሀሳብ ለሀሳብ እንዲለዋወጡ የማድረጉን ሆኔታ መምህራን ተጠይቀው ሲመልሱ 1(33%) መምህር "ሁሉጌዜ " 2(67%) ደግሞ "አብዛኛውን ጊዜ" እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል።ነገር ግን በተደረገው ተከታታይ የክፍል ዉስጥ ምልከታ መረጃ መሰረት፤ ይህን ተግባር ከአንድ መምህርት በስተቀር ሌሎቹ መምህራን ሲተገብሩት አልታዩም። የንግግርን ተግባር በማከናወን ይበልጥ የሚታመነው ተማሪዎችን ከቢጤዎቻቸው ጋር በመመደብ በተወሰነ ርዕስ ጉዳይ ላይ ሀሳባቸውን በቡድኑ መሪ አማካኝነት እንዲያቀርቡ ቢደረግ ተመራጭነት አለው።

**ሠንጠረዥ 4.5. የንግግር ክሂል ትምህርት የልምምድ ሂደትን በተመለከተ ከተማሪዎች ምላሽ የተገኘ መግለጫ**

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን ያቅተኛል | | አልስማማም | | በፍፅም አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 5 | በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ውይይት፣ ክፍሉ በአንድነት በመሆን ወዘተ የንግግር ክሂል ተግባርን በክፍል ውስጥ የመከናወኑ ሁኔታ? | 32 | 35.6 | 21 | 23.3 | 12 | 13.3 | 13 | 14.4 | 12 | 13.3 |
| 6 | በግል፣ በጥንድ፣በሶስትዮሽ፣ በቡድን፣ ወዘተ የንግግር ክሂል ተግባራትን እየተዘዋወሩ በመከታተል ያበረታታሉ? | 23 | 25.6 | 29 | 32.2 | 16 | 17.8 | 13 | 14.4 | 9 | 10 |
| 7 | በክፍል ውስጥ ንግግርን በሪፖርት፣ በጭውውት፣ በክርክር፣ በውይይት መልክ ተግባራቱን መለማመዱ የንግግር ችሎታን አጉልብቷል? | 35 | 38.9 | 34 | 37.8 | 11 | 12.2 | 6 | 6.7 | 4 | 4.4 |
| 8 | በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የንግግር ክሂል ተግባራት ከተማሪው የህይወት ልምድ ጋር የተቆራኙ ናቸው? | 21 | 23.3 | 32 | 35.6 | 25 | 27.8 | 7 | 7.8 | 5 | 5.5 |

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው ተማሪዎች የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ ሲቀርብ በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ውይይት ይለማመዱ ወይም አይልማመዱ እንደሆነና ልምምዱን ሲያከናውኑ መምህራን ክትትልና ድጋፍ ያደርጉ ወይም አያደርጉ እንደሆን ለመፈተሽ ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኞቹ ተማሪዎች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል 35.6%ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 23.3% ተማሪዎች እስማማለሁ፣13.3% ተማሪዎች ለመወሰ ንእቸገራለሁ፣14.4%

ተማሪዎች አልስማማም፣13.3% ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡

በተደረገው ተከታታይ ምልከታ መረጃ መሰረት ይህንን ተግባር የተገበሩ መምህራን ሁለት ሲሆኑ፤ሌላ መምህር ሲተገብር አልተስተዋለም፣ምናልባትም ተማሪዎቹ በሌላ ክሂል የተገበሩትን የንግግር ክሂል ልምምድ አድርገው የወሰዱ ሊሆን ይችላል፡፡በሌላ በኩል የንግግር ክሂል ተግባራት ሲከናወኑ መምህራኑ እየተዘዋወሩ በመከታተል ተማሪዎችን ያበረታታሉ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሰጡት 25.6% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 32.2% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 17.8% ተማሪዎች ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 14.4% አልስማማም፣10% ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡

ከላይ በተደረገው ተከታታይ ምልከታ መረጃ መሰረት ከአንድ መምህርት በስተቀር ተግባሩን ሲያከናውኑ አልተስተዋሉም፡፡ተማሪዎችን በቡድንና በጥንድ ስንመድብ ስብጥሩን በደንብ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ለልምምዱ ተማሪዎች ያላቸውን ችሎታ በመገምገም ምድቡ ከሶስቱም የተማሪዎች ደረጃ ቢሆን የተሻለ ይሆናል፡፡

ተማሪዎች የንግግር ትምህርቱን በተለያየ መልኩ መለማመዱ(በሪፖርት፣ጭውውት፣ክርክር፣ ውይይት) የንግግር ችሎታን አጎልብቷል ተብለው ሲጠየቁ 38.9% በጣም እስማማለሁ፣ 37.8% ተማሪዎች እስማማለሁ፣12.2%ለመወሰን ይቸግረኛል 6.7% ተማሪዎች አልስማማም ብለው ሲመልሱ 4.4% ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚቀርብላቸው የንግግር ክሂል የልምምድ ተግባራት ከራሳቸው የህይወት ልምድ ጋር የተቆራኙ መሆኑን ተጠይቀው 23.3% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 35.6% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 27.8% ለመወሰን እቸገራለሁ፣7.8%አልስማማም በማለት ሲመለሱ 5.5%ተማሪዎች ደግሞ በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ የንግግር ክሂል ልምምዱ ሲከናወን የሚመረጠው ርዕስ በተማሪዎች ቢሆን ልምምዱን ቀላልና የተሳካ ያደርገዋል፡፡በመምህራን ቃለ መጠይቅ መልስ ላይ እንደሚያሳየው ይህንን ተግባር ሁል ጊዜ የሚያከናውኑ አንድም የለም በተጨማሪም በምልከታውም ላይ ሲተገበር የታየው ከመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በወጡ ርዕስ ጉዳይ ላይ ተማሪዎች ሲከራከሩ ተስተውሏል፡፡ ስለዚህ ይህ አተገባበር በጣም ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ የንግግር ክሂልን በልምምድ ተግባር ወቅት ስንመለከት ከቃለ መጠይቅ፣ ከጽሁፍ መጠይቅና ከምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየን የውይይትም ሆነ የክርክር ርዕስ የተማሪውን የህይወት ገጠመኝ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ የልምምዱ ተግባር የሚጠበቀውን ያህል እንዳልሆነ ተመልክተናል፡፡ በሌላ በኩል የልምምዱን ተግባር በጥንድ፣ በቡድንና በግል የማከናወን ሂደት ከጽሁፍ ፣ከቃለ መጠይቁም ሆነ ከምልከታው ምላሽ እንደተረዳነው በጥሩ ሁኔታ እነደተከናወነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

### *4.1.3 የንግግር ክሂል ትምህርት ሲተገበር በአፍልቆት ወቅት የሚታየውን ውጤት መፈተሽ*

**ሰንጠረዥ 4.6 ተማሪዎች በአፍልቆት ወቅት ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ መምህሩ ያመቻቹበትን ሁኔታ ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ መግለጫ**

| ተራ ቁ | የማስተማር ዘዴው ትግበራ | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶ ኛ |
| 17 | የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ የሚያዩትን ነገር በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ይደረግ ነበር? | ___ | ___ | 6 | 100% |
| 18 | የንግግር ተግባራቱ ተማሪዎችን በቀላሉ እና በነፃነት ሊያግባባ የሚችል ዐውድ በመፍጠር የተከናወኑ ናቸው? | ___ | ___ | 6 | 100% |
| 19 | ውይይት እና ክርክር በማዘጋጀት የንግግር ተግባር እንዲከናወን ተደርጓል? | 6 | 100% | ___ | ___ |
| 20 | ተማሪዎች ስህተት ሲፈጽሙ እርማቱ በወቅቱ ይሰጥ ነበር? | ___ | ___ | 6 | 100% |

Harmer(2007) ተማሪዎች በቡድን ይቀመጣሉ ለእያንዳንዱ ቡድን ተከታታይነት ያላቸው መልዕክት አዘል ስዕሎች ይሰጣል፤ ቡድኖቹ ስዕሎቹን ከተመለከቷቸው በኋላ ስእሎቹ ይሰበሰባሉ፤ ከዚያም ከመጀመሪያዎቹ ቡድኖች አንዳንድ አባል የያዙ ሌሎች አዳዲስ ቡድኖች ይደራጃሉ፡፡አዲሶቹ ቡድኖችም ቀደም ሲል ያዩት ስዕላዊ መግለጫ ምን መልእክት እንደሚያስተላልፍ ይናገራሉ፡፡ በመጨረሻም በእያንዳንዱ ቡድን የቀረበው ታሪክ ተመሳሳይ ሀሳብ የያዘ መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ ቡድኖች የየራሳቸውን ታሪክ ለክፍል ያቀርባሉ፡፡ ተግባራቱ በሚቀርብበት ጊዜም የሚቀርበው ተግባራት ለተገልጋዮች ህይወት ቅርበት ያላቸው

መሆን እንደሚገባቸው ያስረዳሉ፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የንግግር ልምምድ ተግባርን ለማከናወን አንዱ መንገድ ስዕሎችን፣ፎቶግራፎችን ወዘተ.. በማዘጋጀት በንግግር መልክ ማቅረብ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ሆኖም ሰሠንጠረዡ እንደሚያሳየው ሁሉም መምህራን በዚህ መልኩ የንግግር ልምምዱን አላካናወኑም ወይም 100%ቱ ተግባራዊ አላደረጉም፡፡በመሆኑም የመማር ማስተማሩ ክንውን በአግባቡ እንዳልተከናወነ ከሰንጠረዡ መረዳት ይቻላል፡፡ተማሪዎች በቋንቋው ተጠቅመው ስለሚያከናውኑት ተግባር በቀላሉና በነፃነት ሊያግባባ የሚችል አውድ እንዲኖር መምህራን ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንዳለባቸው Harmer(1995) ይገልፃሉ፡፡ ሆኖም ግን በመማር ማስተማሩ ሂደት የንግግር ተግባራቱ ተማሪዎችን በቀላሉና በነፃነት ሊያግባባ የሚችል አውድ በመፍጠር የተከናወኑ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡ የክፍል ውስጥ ምልከታው መረጃ እንደሚያመላክተው 100% ይህንን ተግባር አላከናወኑም፤ ስለዚህም ይህ የልምምድ ተግባር የተሰጠው ትኩረት አለመኖሩን ከመረጃው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የንግግር ልምምድ ተግባርን በውይይትና በክርክር ሁሉም መምህር ተግብረዋል፡፡ ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው 100% የመማር ማስተማሩ ሂደት ተከናውኗል፡፡

የንግግር ክሂልን የማስተማር ዓላማ እንደ Harmer(1995) ገለጻ ተማሪዎች በቋንቋው ተጠቅመው ሀሳባቸውን መግለጽ እንዲችሉ ነው፡፡ በመሆኑም ዘመናዊ በሆነ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ዘዴ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በዚህም በቋንቋው የመጠቀም ችሎታቸውን ያዳብሩ ዘንድ አስፈላጊው ጥረት ሁሉ ቢደረግ ተገቢ ነው፡፡ ይህም የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡- ተገቢ ቃላትን በተገቢው ቦታ መጠቀም እንዲችሉ፣አስተያየታቸውን በማስረጃ አስደግፈው ማቅረብ እንዲችሉ፣ ግላዊ አመለካከቶችን በንግግር ነጻ ሆነው ሀሳባቸውን እንዲገልጹ እና ኢ-መደበኛ አነጋገርን አስወግደው መደበኛ የአነጋገር ስልትን እንዲጠቀሙ ይረዳቸዋል በማለት አስቀምጠዋል፡፡

ከምልከታው በተገኘው መረጃ መሰረት መምህራን በልምምድ ወቅት ተማሪዎችን የመርዳትና የማገዝ ስራ መስራት እንዳለባቸው ይታወቃል፡፡ በምልከታው ወቅትም ተማሪዎች ሀሳባቸውን በሚገልጹበት ወቅት ብዙ ስህተቶች ይከናወኑ ነበር፡፡ለምሣሌ፡- በአንድ ክፍል በሚሰጠው የክርክር ሂደት ላይ ተማሪዎች ተራቸውን ሳይጠብቁ የመናገር ሁኔታ፣ ከክርክሩ

ርዕስ አፈንግጦ የመውጣት፣ የተቃራኒ ተከራካሪ ቡድንን ያለማክበር እና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ተከስተው በመምህሯ የተሰጠ እርምት አልነበረም፡፡ ሰንጠረዡ እንደሚያመላክተው ተማሪዎች ስህተት ሲፈጽሙ እርምቱ በወቅቱ አለመሰጠቱንና ሁሉም መምህራን ይህንን ተግባር አለማከናወናቸውን ያሳየናል፡፡

### 4.1.3.1.ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ ማድረግ አለማድረጋቸውን ለማወቅ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ ምላሽ የተገኘ መግለጫ

ጥያቄ.ቁ.12. የንግግር ተግባሩ ከቀረበና በዚያ ላይ ከተለማመዱ በኋላ ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ ያበረታታሉ?

በዚህ የንግግር ክሂል ትምህርት የመጨረሻ ደረጃ ልምምዱን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች በራሳቸው የቋንቋ እውቀት በመጠቀም ሀሳባቸውን አፍልቀው የሚገልፁበትን መንገድ መምህሩ የሚያመቻችበትን ሁኔታ መፍጠር ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንፃር የቃለ መጠይቁ ምላሽ እንደሚያመለክተው ሁለት(67%) መምህራን "አብዛኛውን ጊዜ" በማለት ሲገልጹ አንድ(33%) መምህር ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" በማለት ተግባሩን እንሚተገብሩ ገልፀዋል፡፡እንደሚታወቀው ተማሪዎች የልምምድ ተግባሩን ካጠናቀቁ በኋላ ሀሳባቸውን ለመግለፅ ምቹ ሁኔታ እንደሚያስፈልጋቸው በክለሳ ድርሳናት ውስጥ የተጠቀሱት የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከመረጃው ምለሽ እነደተረዳነው መምህራን "ሁልጊዜ" ሲተገብሩት አልታየም፡፡

ጥያቄ.ቁ.13. ተማሪዎች ከክፍል ውጪ ሰዎችን ጠይቀው ወይም ምልከታ አድርገው እና የተለያዩ ፅሁፎችን አንብበዉ በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ያደርጋሉ?

ተማሪዎች ከቀረበላቸው ከመጽሀፉ መልመጃ ውጪ ሰዎችን ጠይቀው ወይም የተለያዩ ትዕይንቶችን ተመልክተው እና ጽሁፎችን አንብበው በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ የማመቻቸቱ ሁኔታ ከቀረበላቸው የቃለ መጠየቅ ምላሽ አንድም መምህር ተግባሩን "ሁልጊዜ" እንዳላከናወነ መረዳት የተቻለ ሲሆን፤ አንድ (33%) መምህር "አብዛኛውን ጊዜ" ተግባሩን እንደሚያከናውን ሲገልጹ፤ ሁለት(67%) መምህራን ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚተገብሩት ገልፀዋል፡፡ይህም በተከታታይ ከተደረገው ምልከታ ምላሽ ጋር ይመሳሰላል፡፡

ጥያቄ.ቁ.14. በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት በተማሪዎቹ ንግግር መሀል ጣልቃ በመግባት እንዴት መናገር እንዳለባቸው እርማት ይሰጧቸዋል?

በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት በተማሪዎች ንግግር መሀል ጣልቃ በመግባት ስህተታቸውን የማረሙን ሂደት መምህራኑ ሲገልፁ፣ አንድ(33%) መምህርት "ሁልጊዜ" ተግባሩን እደምታከናውን ስትገልፅ ሁለት(67%) መምህራን ደግሞ "አብዛኛውን ጊዜ" ሂደቱን እንደሚያከናውኑ ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ግን በተከታታይ በተደረገው ምልከታ መረጃ መሰረት አንድም መምህር በተማሪዎች ንግግር መሀል ጣልቃ በመገባት ስህተታቸውን የማረሙ ሁኔታ አልታየም፡፡

ጥያቄ.ቁ.15. የንግግር ክሂል ትምህርቱ ከመጠናቀቁ በፊት ተማሪዎቹ ጥያቄ እንዲጠይቁ ያበረታታሉ?

የዕለቱ የንግግር ክሂል ትምህርት ከመጠናቀቁ በፊት ተማሪዎች ያልገባቸውን ጥያቄ እንዲጠይቁ የማበረታቱን ሁኔታ መምህራን ተጠይቀው ሁለት(67%) መምህራን ሁልጊዜ ተግባሩን እንደሚያከናውኑ ሲገልጹ አንድ(33%) መምህር ደግሞ ተግባሩን "አብዛኛው ጊዜ" እንደሚተገብር ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም በተከታታይ በተደረገው ምልከታ አንድም መምህር ይህንን ተግባር ሲያከናውን አለመታየቱን ተገንዝበናል፡፡

ጥያቄ.ቁ.16. ተማሪዎች ስህተትን እንደ አንድ የመማሪያ መንገድ አድርገው እንዲቆጥሩ ያስገነዝባሉ?

ተማሪዎች የንግግር ክሂል ትምህርቱን ተግባር ሲያከናውኑ ስህተት እንደ አንድ የመማሪያ መንገድ አድርገው እንዲቆጥሩ የማስገንዘቡን ሁኔታ ተጠይቀው መምህራን ሲገልፁ አንድ(33%)መምህርት "ሁል ጊዜ" እንደምትፈፅመው ስትገልፅ ሁለት (67%) መምህራን ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚያከናውኑ ገልፀዋል፡፡ ሆኖም ግን ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ሀሳባቸውን በነፃነት ለማቅረብ ከሚያደርጓቸው አንዱና ዋነኛው ምክንያት በተሰጣቸው ርዕስ ዙሪያ የመሰላቸውን ሀሳብ እንዳይገልፁ እንሳሳታለን የሚል ፍራቻ ይታይባቸዋል፡፡ይህ ችግር ለመቅረፍ መሳሳት ትምህርት መሆኑንና ቢሳሳቱም የመማር ማስተማሩ አንዱ መሆኑን ገልፆ መምህሩ ሚናውን መወጣት ይኖርበታል፡፡

ጥያቄ.ቁ.17. ተማሪዎቹ ስህተታቸውን እርስ በእርስ እንዲተራረሙ ያመቻቻሉ?

ተማሪዎች ስህተታቸውን እርስ በእርስ እንዲተራረሙ የማመቻቸቱን ሁኔታ ተጠይቀው አንድ(33%)መምህር "ሁልጊዜ" ተግባሩንእንደሚተገብር ሲገልጽ ሁለት(67%) መምህራን ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" ተግባሩን እንደሚያከናውኑ ገልፀዋል፡፡በተከታታይ በተደረገው ምልከታ ላይም መረጃው የሚያመለክተው መምህራኑ ከሰጡት መረጃ ጋር ተመሳሳይነት ይታይበታል፡፡

ጥያቄ.ቁ.18. በቀረበው የንግግር ክሂል ትምህርት ላይ የማሻሻያ ሀሳብ ይሰጣሉ?

በመጨረሻም ለቀረበው የንግግር ክሂል ትምህርት የማሻሻያ ሀሳብ የመስጠት ሁኔታ ተጠይቀው ሁለት(67%) መምህራን "ሁልጊዜ" ተግባሩን እንደሚያከናውኑ ሲገልፁ አንድ(33%) መምህርት ደግሞ "አብዛኛውን ጊዜ ተግባሩን እንደታምከናውን ገልጻለች ፡፡

## ሰንጠረዥ . 4.7. የአፍልቆት ደረጃ የንግግር ክሂል አቀራረብን በሚመለከት የተማሪዎችን ምላሽ የሚያሳይ መግለጫ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | መወሰን ያቅተኛል | | አልስማማም | | በፍፁም አልስማማም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 9 | በጥንድ፣በቡድን ወዘተ በመሆን የንግግር ክሂል ተግባራትን በመለማመድ እና በመከታተል የንግግር፣ የጭውውት ፣ የክርክር የውይይት ስርአት እንዲዳብር ተደርጓል? | 25 | 27.8 | 36 | 40 | 12 | 13.3 | 9 | 10 | 8 | 8.9 |
| 10 | የንግግር ተግባራትን ስታከናወኑ ሀሳብችሁን በነፃነት እንድትገልፁ ተደርጓል? | 40 | 44.4 | 25 | 27.8 | 12 | 13.3 | 7 | 7.8 | 6 | 6.7 |
| 11 | በጥንድ፣ በቡድን በመሆን ቃለ መጠየቅ ማድረግ ስዕላዊ መግለጫዎች በሚያስተላልፉት ሀሳብ ላይ መወያየትና መከራከር እንዲሁም ሀሳብን ያለፍርሀት ለመግለፅ ተችላል? | 24 | 26.7 | 25 | 27.8 | 21 | 23.3 | 11 | 12.2 | 9 | 10 |
| 12 | የጭውውት ፣ የክርክር፣ የውይይት ተግባራት በክፍል ውስጥ ከቀረቡ በኋላ በማጠቃለል ያለምንም ፍርሀት አስተያት እሰጣለሁ? | 25 | 27.8 | 31 | 34.4 | 12 | 13.3 | 14 | 15.6 | 8 | 8.9 |
| 13 | ስህተታችን በቀጥታ ከመናገር ይልቅ እርስበርስ እንድንተራረም ይደረግ ነበር? | 28 | 31.1 | 26 | 28.9 | 15 | 16.7 | 15 | 16.7 | 6 | 6.6 |
| 14 | ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ ይበረታታሉ? | 32 | 35.6 | 30 | 33.3 | 16 | 17.8 | 5 | 5.6 | 7 | 7.7 |
| 15 | የንግግሩ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል ይሰጣሉ? | 40 | 44.4 | 20 | 22.2 | 12 | 13.3 | 10 | 11.2 | 8 | 8.9 |

የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ ተማሪዎች እንዲማሩ የሚደረግበት ምክንያት ንግግር፣ ክርክር፣ ውይይት ወዘተ… ሲያደርጉ መረጃ አሰባስበው፣ አደራጅተውና ተለማምደው ሀሳባቸውን ማግለጽ እዲችሉና የእነዚህ ተግባራትን ቅድመ ሥርአት እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን የንግግር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ማቅረባቸው እና መከታተላቸው የጭውውት፣የክርክር፣የውይይት ወዘተ ስርዓት ለማወቅ የረዳቸው መሆኑንና አለመሆኑን የሚመለከት ሲሆን፣መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች ውስጥ 27.8% በጣም እስማማለሁ፣40% እስማማለሁ፣ 13.3% ተማሪዎች ለመወሰን ይቸግረኛል 10% አልስማማም በማለት ሲመልሱ 8.9% ተማሪዎች ደግሞ በፍጹም አልስማምም በማለት ተግባራቱን አለመፈጸማቸውን ገልጸዋል፡፡

ይህ ማለት ለምሳሌ በክርክር ጊዜ ክርክሩ ተራ በተራ ይካሄድ ወይስ እያጠናቀቁ የመሄድ ስልትን እንደሚከተል ማወቅ አንዱ የክርክሩ ስርዓት ሲሆን፣ በክርክሩም ሀሳብ እንደተዘረጋ ከተከራካሪዎቹ ሀሳብ ሲቀርብ ሌሎች የሚያዳምጡ መሆኑን፣ጥያቄና የተቃራኒ ሀሳብን ውድቅ ማድረጊያ ሀሳብ ቀርቦ ፣ውሳኔ በድምጽ ወይም በዳኞች የሚሰጥ መሆኑን ማወቅ ከተከራካሪዎች የሚጠበቅ ነው፡፡ስለሆነም አብዛኛቹ ተማሪዎች ክርክርና ጭውውት በክፍል ዉስጥ ማቅረባቸው እነዚህንና ሌሎች መሰል ስርዓቶችን ለማወቅ እንዲረዳቸው አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህ ውጭ የሆኑት ተማሪዎች ግን ግልጽ ግንዛቤ የሌላቸውና በሀሳቡ የማይስማሙ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የንግግር ተግባራትን ስታከናውኑ ሀሳባችሁን በነጻነት እንድትገልጹ ተደርጓል ወይ? ተብለዉ ለተጠየቁት ጥያቄ ሲመልሱ 44.4% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣27.8% ተማሪዎች እስማማለሁ፣13.3 ተማሪዎች ለመወሰን ይቸግረኛል፣7.8%ተማሪዎች አልስማማም፣ 6.7% ተማሪዎች ደግሞ በፍጹም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚሁ ጥያቄ ጋር ተያያዥነት ያለዉ ጥያቄ የተለያዩ የንግግር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ መለማመዳቸው ሀሳባቸውን ያለ ፍርሃት ለመግለጽ ያስቻላቸው ወይም ያላስቻላቸው መሆኑን የገለፀ ነበር? 26.7% እና 27.8% ተማሪዎች ማለትም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሀሳባቸውን ያለፍርሀት መግለጽ መቻላቸውን ገልጸዋል፡፡

ሌሎቹ 23.3% መወሰን እንዳቃታቸውና 12.2% እና 10% ተማሪዎች አለመስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ግን በተከታታይ በተደረገው ምልከታ መረጃ መሰረት መገንዘብ የተቻለው ማንኛውም መምህር ተማሪዎች ፍርሃታቸውን እንዲያስወግዱ ተግባራትን ሲያከናውኑ አልታዩም፡፡ እንዲሁም የመምህራን ቃለ መጠየቅ መረጃ እንደሚያሳየው ተግባራቱን ሁልጊዜ እንደማያከናውኑት ለመረዳት ተችሏል፡፡

ተማሪዎች የጭውውት ፣የክርክር ፣የውይይት ተግባራት በክፍል ውስጥ ከቀረቡ በኋላ በክፍለ ጊዜው ማጠናቀቂያ ላይ አስተያየት መስጠታቸውን ተጠይቀው 27.8% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 34.4% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 13.3% ለመወሰን እቸገራለሁ፣ 15.6% ተማሪዎች አልስማማም እና 8.9% ተማሪዎች ደግሞ በፍጹም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡በንግግር ክሂል አቀራረብ የሚደረግ የማጠቃለያ ሀሳብ አሰጣጥ ተማሪዎች በሂደቱ እንዲሳተፉና እርስ በእርስ እንዲተራረሙ ከተደረገ በኋላ በመምህራን ቢጠቃለል የተማሪዎች የእርስ በእርስ ተራክቦና በራስ የተማመን ስሜት እየጐለበተ ሊሄድ ይችላል፡፡

እንደ Sesnan(1997)ገላፃ ብዙ ሰዎች በቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ሲተራረሙ ስሜታቸው ይጐዳል ብለው ያስባሉ፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች በዕለት ተዕለት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንደሚታየው እርስ በርስ ይተራረማሉ፤ መተራረሙንም በደስታ ሲቀበሉት ይታያል ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ መሰረተ ሀሳብ በመነሳት ተማሪዎች ስህተታቸውን እርስ በእርስ እንዲተራረሙ ይደረጋል ወይ? ተብለው ከተጠየቁ ተማሪዎች መካከል 31.1% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 28.9% ተማሪዎች እስማማለሁ፣16.7% ተማሪዎች ለመወሰን እቸገራለሁ፣16.7%ተማሪዎች አልስማማም፣6.6%ተማሪዎች ደግሞ በፍጹም አልስማማም በማለት መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ሆኖም በተደረገው ተከታታይ ምልከታ እርስ በርሳቸው ሲተራረሙ አልታዩም፡፡ እንዲሁም የመምህራን የቃለ መጠይቅ ምላሽ እንደሚያሳየው ከአንድ መምህርት በስተቀር ሌሎቹ አንዳንድ ጊዜ እንደሚተገብሩት ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ ይበረታቱ ነበር? ተብለው ተጠይቀው 35.6% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣ 33.3% ተማሪዎች እስማማለሁ፣ 17.8% ተማሪዎች ለመወሰን እቸገራለሁ 5.6% ተማሪዎች አልስማማም ሲሉ 7.7% ተማሪዎች ደግሞ በፍጹም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ እንዲሁም የንግግሩ ተግባር

በሚከናወንበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል ይስጥ ነበር ለሚለው ተማሪዎች ሲመልሱ 44.4% ተማሪዎች በጣም እስማማለሁ፣22.2% እስማማለሁ ፣ 13.3% ተማሪዎች ለመወሰን ያቅተኛል ፣11.2% ተማሪዎች አልስማማም በማለት ሲመልሱ 8.9% ተማሪዎች በፍጹም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡

በጥቅሉ ሲታይ ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ በተወሰነ መልኩ ልዩነት ቢኖረውም ከሶስቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎች ውጤት ብዙም የጎላ ልዩነት አይታዩበትም፡፡ምልከታ በተደረገበት ጊዜ በአፍልቆት ደረጃ በተለይ በአንድ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች የእርስ በእርስ መስተጋብር በቀረበው የክርክር ርዕስ ላይ ተከራካሪዎቹ የክርክርሩን ደንብ ባለማወቅ ደንብ ሲጥሱ እንደነበር የተመልካቾቹ ስርዓት ያለመያዝ እና ያለመደማመጥ ሁኔታ እንደ ነበር ታይቷል፡፡ የመከራከር እድል ካገኙ ተማሪዎች መካከል የተወሰኑት ተማሪዎች በቂ ዝግጅት የማድረግ ፣ ሀሳባቸውን አደራጅተው የመናገር ፣ የሀሳብ ማሟያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ሀሳብ የማስተላለፍ ችግር ከልምምድ ማነስ የተነሳ ይታይባቸው እንደ ነበር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

## 4.2. የመረጃዎቹ ትንተና ማብራሪያ

### 4.2.1. የንግግርን ክሂል ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶች ክንውን

በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረበው የ ዘ ጠ ነ ኛ ክ ፍ ል የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ በአስሩ ምዕራፎቸ ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ መልመጃዎችን አካቷል፡፡ ይህ የሚያመለክተው ለንግግር ክሂል ትኩረት መሰጠቱን ነው፡፡ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረቡት ይዘቶችና ክንውኖች ሁሉም ማስተማሪያ መሳሪያዎችን መስረት ያደረጉ ናቸም፡፡ ሆኖም የንግግር ክሂልን ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ በተማሪዎች ተመርጠው የሚቀርቡና ከራሳቸው የህይወት ገጠመኝ ጋር የተቆራኘ ቢሆን ትምህርቱን በርትተው እንዲማሩ ያነሳሳቸዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ይዘቶችና ክንውኖች ብቻቸውን በንግግር ሀሳብን የመግለፅ ችሎታንና ተግባቦትን የመፍጠር ብቃትን የማያዳብሩ መሆናቸውን አጥኝዋ በሰበሰበቻቸው መረጃዎች አማካኝነት ደርሳበታለች፡፡

## 4.2.2. የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ትግበራ

ተማሪዎች በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ ማድረግ የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ ነው። ከእነዚህ ክሂሎች አንዱ ደግሞ ንግግር መሆኑ ቀደም ተብሎ ተገልጿል። በመሆኑ ንግግርን በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩ ሂደት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ሊዳብር ይገባል። ስለዚህ በንግግር ክሂል ትምህርት የአቀራረቡን፣ የልምምዱን እና የአፍልቆት ሂደቱ በተግባር ላይ እንዲውሉ የሚያስችል የመማር ማስተማር ስልትና መልመጃዎች በበቂ ሁኔታ መመረጥና መደራጀት አለባቸው።በመማር ማስተማሩ ሂደት የትምህርት አቀራረብ መምህሩ ወደ ዋናው ተግባር ከመግባቱ በፊት የተማሪዎችን ትኩረት ለመሳብና ውስጣዊ ፍላጎታቸውን ለማነሳሳት የማነቃቃት ተግባር መፈፀም ይገባዋል።ይህንን በማድርጉም በቋንቋው ተጠቅመው ሀሳባቸውን በንግግር እንዲገልጹ ከማበረታታቱም ባሻገር የመማር ማስተማሩ ሂደቱ ውጤታማ ይሆናል። የማነቃቃት ሥራ ትምህርት ለመጀመር ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የንግግር ክሂል ማስተማር ደረጃዎች እጅግ ጠቃሚ መሆኑን አብዛኞቹ ምሁራን ይስማሙበታል። ይሁን እንጂ ከክፍል ውስጥ ምልከታው የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው ለዚሁ ተግባር ብዙም ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን ነው።

ተግባቦታዊ አቀራረብ ተማሪዎች በቋንቋው ተጠቅመው በተለያዩ ማህበራዊ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሀሳባቸውን በመግለጽ በቂ ልምምድ የሚደረግበት የአቀራረብ ስልት ነው። በተጨማሪም የተማሪዎች መስተጋብር እንዲጨምር ፍንጭ ሰጪ ሀሳብና የተለያዩ ስዕሎች፣ፎቶግራፎች፤ ካርታዎች ወዘተ.. በተጨባጭ በክፍል ውስጥ በማምጣት ተነሳሽነታቸውንና ፍላጎታቸውን ባገናዘበ መንገድ ተማሪዎች እንዲናገሩ እና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ መምህራን ያደረጉት ጥረት ደካማ እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ።

መምህራን አልፎ አልፎ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ንግግርን የሚለማመዱበትን ክንውን የሚሰጡ ቢሆንም ተማሪዎቹ በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን እርስ በርሳቸው ሀሳብ ለሀሳብ እንዲለዋወጡ፣ሌሎች የሚያስተላልፉትን ሀሳብ መረዳት እንዲችሉ፣ እንዲከራከሩ፣ እንዲወያዩ ወዘተ… የማድረጉ ሁኔታ ዝቅተኛ እንደሆነ ለማየት ተችሏል።

የምልከታው፣የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ መረጃ በግልጽ እንዲሚያሳየው ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር የመግለጽ ችሎታቸውንና ተግባቦታቸውን ለማዳበር የሚያስችላቸውን በተግባር የሚለማመዱበት ሁኔታ ሲታይ በተወሰኑ ተማሪዎች ላይ ብቻ በማተኮር ሌሎች ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን በተገቢው መንገድ እንዳይለማመዱ መደረጋቸውን መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡መምህራኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪው ሀሳቡን በንግግር መግለጽ የሚችልበትን መንገድ በጥንድ ወይም በቡድን ንግግርን የሚማሩበትን ስልት የማመቻቸት ሁኔታ በአብዛኛው እንዳላከናወኑ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5.ማጠቃለያ ፣መደምደሚያ  እና የመፍትሄ ሀሳቦች

### 5.1.ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በምስራቅ ወለጋ ዞን በጉደያ ቢላ ወረዳ በሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ተምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንግግር ክሂል አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡ይህንን አላማ ዳር ለማድረስ ጥናቱ ገለጭ የምርምር ንድፍን ተጠቅሟል፡፡በጉደያ ቢላ ወረዳ በሚገኙ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሶስት መምህራን በጠቅላይ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡እንዲሁም ከእነዚህ ሶስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ዘጠና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በቀላል የዕጣ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡መረጃዎችንም ለማግኘት ምልከታ‹፣የፅሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘው መረጃ በአይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴ ተተንትኖ የጥናቱ ውጤቱ ተገኝቷል፡፡

### 5.2. መደምደሚያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በምስራቅ ወለጋ ዞን በጉደያ ቢላ ወረዳ በሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ተምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንግግር ክሂል አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ መረጃዎች ተሰብስበው ፣ተደራጅተው፣ ተተንትነዋል፡፡ የተገገኘው ውጤት ማብራሪያ ተሰጥቶበት መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡

- ✓ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ንግግርን  በማስተማር ሂደት ተማሪዎች ትርጉም ባለው መንገድ ችሎታቸው እንዲዳብር፤የተለያዩ የንግግር ክሂል ማስተማሪያ መንገዶችን በመጠቀም እያንዳንዱ መምህር ራሱን በማዘጋጀት ረገድ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይሁን እንጅ በአቀራረብ ደረጃ  መምህሩ ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ስነ ዘዴን በመጠቀም ጥሩ የመማር ማስተማር ሁኔታን  በክፍል ውስጥ እንዲፈጠር አላመቻቸም ወደሚል  መደምደሚየ ላይ ሊያደርስ የሚችል ነው ፡፡

- ✓ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ንግግላርን ለማስተማር ከተማሪዎች የህይወት ገጠመኝ ጋር የተገናኙ ርዕሰ ጉዳዮችን፤የማነቃቂያ ስቶችን ስላልተጠቀሙ ተማሪዎች ቶሎ የመሰላቸት፣ ለመሳተፍ ፍላጎት ማጣት አዝማሚያ በተማሪዎች ላይ መታየቱንና ለቋንቋ ተግባቦት ዝቅተኛ ቦታ አላቸው ወደሚለው ድምዳሜ ያደርሳል ፡፡

- ✓ የመረጃው ውጤት እንደሚያመለክተቀው በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶችና ክንውኖች መምህር ተኮር፣ የተማሪዎችን ነባራዊ ሁኔታ በሚያሳይ ርዕስ ላይ ያልተመሰረቱና በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ብቻ ተመርኩዘው የቀረቡ በመሆናቸው የተማሪዎቹን ትኩረት እንዳይስብ በማድረግ ለንግግር ክሂል መዳበር እንቅፋት ይሆናል ለማለት ይቻላል፡፡

- ✓ እንዱሁም የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶችና ክንውኖች ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን የማያበረታቱ እና መምህር መር አቀራረብን መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው ክሂሉ በአግባቡ እንዳይተገበር በተማሪዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ ውጤቱም ለተግባቦታዊ ክሂሎች እንቅፋት የሚሆን ነው፡፡

በአጠቃላይ የጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው የቀረበው የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ ትግበራ የተማሪዎችን ስሜትና ፍላጎትን የላገናዘበ በመሆኑ ነፃ ሆነው እንዲናገሩ የማያበረታታ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ የምንረዳው የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበር መምህራን በቂ ጊዜ ወስደው፣የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ግልፅ አላማን አንግበው ሥራውን እንዳላከናወኑት ያስገነዝበናል፡፡

## 5.3. የመፍትሄ ሀሳቦች

ለጥናቱ መነሻ ከሆኑ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ የታዩ ችግሮች ለወደፊቱ ይፈቱ ዘንድ መፍትሄ መጠቆም ነው፡፡ ስለሆነም ጥናቱ ያነሳቸውን ጥያቄዎች እና ግኝቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት **የመፍትሄ ሀሳቦች** ቀርበዋል፡፡

- መምህራን የንግግር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት መነሻ ቢያደርጉ፤
- ተማሪዎች ወደ ዋናው የንግግር ክሂል ትምህርት ከመግባታቸው በፊት የማነቃቂያ ተግባር ቢሰጣቸው፤
- የንግግር ክሂል ተግባር ከመከናወኑ በፊት የትምህርቱ አላማ በዝርዝር እንዲቀርብ ቢደረግ፤
- የንግግር ክሂልን ለማሳደግ የቀረቡትን ተግባራት ለማለማመድ የሚሰጠው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ከመልመጃዎቹ ስፋት ጋር እየታየ ቢመጠን፤
- ጭውውት፣ውይይት፣ ክክርክር በተጨማሪ የግልና የጥንድ ስራን የሚያበረታቱ እንደ ታሪክ ነገራ፣ ቃለመጠይቅ የመሳሰሉ ተግባራት በቀጣዩ ዝግጅት እንዲካተቱ ትኩረት ቢሰጣቸው፤
- የተማሪዎቹን የንግግር ክሂል ለማሳደግ መምህራን ከተማሪዎች የህይወት ተሞክሮ ጋር የተያያዙና ሳቢነት ያላቸው ርእሶች ከተለያዩ ምንጮች(ከጋዜጣ ወይም መጻህፍት)ቀንጭቦ ወደ ክፍል ለማምጣት ቢሞክሩ፤
- መምህራን ተማሪዎቻቸው ያሉባቸውን የንግግር ግብዓት ማጣት ችግር መቅረፍ ይችሉ ዘንድ ጋዜጦችን፣መጻህፍትን ወዘተ… አንብበው እንዲመጡ ቢያበረታቱ፤
- ለንግግር የማይደፍሩ ተማሪዎችን መምህራን የተለየ ትኩረት በመስጠት በልምምድ ወቅት ከፍተኛ ክትትል ቢያደርጉላቸው፤
- በአፍልቆት ትምህርት ወቅት የተወሰኑ ተማሪዎችን ብቻ ከማሳተፍ ይልቅ ሁሉም ተማሪዎች ተግባሩን እንዲያከናውኑ በማድረግ አብዛኛውን ጊዜ የሚታየው የመምህር መር የትምህርት አቀራረብ ዘዴን ቀንሶ ተማሪ መር የመማር ማስተማሩ ሂደት ተግባራዊ ቢሆን፤
- የንግግርን ክሂል ለማሳደግ የሚረዱ ተግባራትን (መልመጃዎች የተማሪዎቸን እድሜ፣ ጾታ፣ የእውቀት ደረጃ፣ የመጡበትን አካባቢና ቋንቋ ወዘተ) ያገናዘቡ

እንዲሆኑ በመጽሀፍት ዝግጅት ወቅት የፍላጎት ዳሰሳ ማድረግ ትኩረት ቢሰጠው፤

- መምህራን ከአዳዲስ ጽንስ ሀሳቦችና ከማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር ለማስተዋወቅ ትምህርት ቢሮ፣የዞኑ ትምህርት ጽህፈት ቤት፣ የወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት፣ መምህራንን የሚመለከቱ ስልጠናዎች እንደአስፈላጊነታቸው ቢያዘጋጁ ቢሰጡ፤

- የመማሪያ ክፍል መጨናነቅ በንግግር ክሂል አቀራረብ አሉታዊ ተጽእኖ ስላለው ተማሪ ክፍል-ጥምርታ መማሪያ ክፍሎች ግንባታ በከተማውና በወረዳው ትምህርት ቢሮ ስታንዳርድ መሰረት እንዲሆን የወረዳው አስተዳደር እና የወረዳው ትምህርት ጽህፈት ቤቶች፣ የአካባቢው ህብረተሰብ እና መንግስታዊ የሆኑ ድርጅቶች ትኩረት ቢሰጡት ከችግሩ በመላቀቅ የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳካ ይሆናል ብላ አጥኚዋ ታምናለች፡፡

## ዋቢ መፅሐፍት


ማረው አለሙ፡፡ (1998)፡፡ <u>የአማርኛ ቋንቋ  ማስተማሪያ ዘዴ</u> ፡፡ አዲስ አበባ ፤ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (2007)፡፡ <u>በስነ-ፅሑፍ ቋንቋ ማስተማር</u>፡፡ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃ.ላ.የተ.ማ

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡ (1981)፡፡ ስነ-ልሳን እና የቋንቋ ማስተማር፡፡የቋንቋዎች እና ጥናት ተቋም፣ አዲስ አበባ፣ ዩኒቨርስቲ፡፡ (ያልታተመ)

አያል ሰው ይታየው፡፡ (2003) ፡፡‹‹ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍት ውስጥ በሚገኙ የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ መማር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተና እና ግምገማ›› የሁለታ ድግሪ መሟያ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የቋንቋዎች ጥናትና ተቋም

እጅጉ ይማም፡፡ (2003) ፡፡‹‹በደብረ ብረሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረብ ግምገማ ፡፡የአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

ያለው እንዳወቀ፡፡(2001)፡፡<u>የምርምር መርሆች አተገባበር</u> ፡፡ ሁለተኛ እትም፡፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት

ጥላሁን ከበደ ፡፡ (2003) ፡፡ ‹‹የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምኅራን የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አተገባበር ፍተሻ›› (በሰሜን ወሎ ዞን በተመረጡ ሦስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)፡፡ የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር  ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፡፡

Alumettu,T.(2018).<u>Developing the Students English Speaking abilities through</u>

Anuradhaa,Rev.&etal.(2014).<u>Methods of Teaching English.</u> Hyderabad ,NeelKamal Publications.

Benter,O.(2015).Teaching Speaking skills in English Language using class room activities in Secondary School level in Eldoret Municipality.

Kenia.Journal of Education and Practice. Vol-6 No. 35

Bygate. M. (1987) .speaking .oxford university press.

Brown &Yule .(1983). <<A Holistic approach toTeaching speaking in the langage class room>> (symposium)

Broum Fate .(1984). Imprving for class room.Interaction. London longman. Group UK limited

Byrne .D. (1976) .Teaching oral English. London Longman

Byrne .D. (1987).Techinque in Class room Interaction.Students Englewood Cliffs:M.printice Hail.

Celce,M.& Olshtain,E.(2000).Discourse and Context in Language Teaching. AGuide for Language Teachers.Cambridge.Cambridge University Press.

Cook.G. (1989). Discourse Oxford University press.

Dedi, Rahaman Nur.(2017).Techniques for Teaching Speaking. in Widya Gama Mahakama University. Vol.2No.1.PP 1-13

Gower,R.,Phillips,D,andwalters.S.(1995)*Teahcing practice hand book*. Oxford.Heinemann.

Harmer .J. (1995).the principle English language Teaching. London: longman.

Harmer .J. (2007). How to teach English. Llondon.longman

Hussien,S.(2017) Factors Affecting the Implementations of Coumminication Language teaching in Libyan Secondary Schools. Doctoral Sheffield Hallam University.

Kedir, Abda.(2017). Assesing The Factors that Affect Teaching Speaking Skills: The Case Robe Teachers College, English Department Second Year Students. Robe,Ethiopia.Journal Vol.3 pp No. 285-295

Kumari, Av.(2014). Methods of Teaching English.Gunture: New Era Publications.

Lewis & siek (1993) .Teaching English 7-12..new yourk America Book Company.

Mariam B.(2015). Factors Effecting Students English Speaking Skills. British.

Journal of art. Vol.2 No.1 Page -18

McDonough.J.andshaw. C(1995) *Materials and Methods in ELT: Ateachers Guide. Oxford*. B.Lack well Publishers Ltd.

Nunan. D. (1991). Tasks for the commumicative classroom. Sydney cambirlge universty press

Paul Nation.(1990).*Improving Speaking fluency*. Vol.17.No.3,pp.377-384,printed Great Britain.

Pressley.M.D&etal.(2007).*Teaching reading journale of education psychology*.Vol.pp.m124.pp129

Rechards .jack.(1994).the context of language teaching. Cambridge. cumbridge university press

Sensnan.(1997). How to teach English. oxford cup.

Shafaat Husain.(2018). Teaching Speaking Skill in Communication Class room. Madda Walabu University. Bale Robe, Ethiopia.

Tricia Hedge.(1996). Teaching and learnig in the laneguae class room. oxford university press.

Ur.p.(1996). Acovrse in language teaching practice and theory. Cambridge universrsity pre

Widdowson H.G(1992).*Teaching Language as communication*.Oxford University Press

Zubizarreta, L. (2017).Action Research to improve speaking skills in official Turist .Guide.Students of Instituto Superior technologic. esdit arequina

## አባሪ አንድ

## ጅማ ዩኒቨርስቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል

## የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር

## የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ

### የክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርት ክንውን ምልከታ መከታተያ ቅፅ/Check list /

ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ዞን____________________ወረዳ______

የትምህርት ቤቱ ስም _________________

ምልከታ የተካሄደበት የክፍል ደረጃ __________________

ምልከታ የተደረገበት ቀን ____________________

ምልከታ የተደረገበት ክ/ጊዜ _________________

ምልከታ የተደረገበት ሰዓት ________________________

በምልከታው ወቅት ይሰጥ የነበረው የትምህርት ርዕሰ______________________

ይህ የምልከታ ቅጽ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል ተግባራት የክፍል ውስጥ አቀራረብን ለመከታተል ታስቦ የተዘጋጀ ነው። በክፍል ምልከታ ወቅት ተግባራቱ ተከናውነው ከሆነ/√/ምልክት "አዎ ከሚለው ላይ ይደረጋል።ተግባራቱ ያልተከናወኑ ከሆነ ደግሞ / X/ ምልክት "አይ" ከሚለው ላይ ይመለከታል።

| ተ.ቁ | የማስተማሪያ ዘዴ<br>ትግበራ | አዎ | አይ |
|---|---|---|---|
| 1 | የተወሰነ ዓላማ ለተማሪዎች ቀርቦ ነበር? | | |
| 2 | የትምህርቱ አቀራረብ የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መሰረት ያደረገ ነበር? | | |
| 3 | በትምህርቱ አቀራረብ የተለያዩ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ቀርበው ነበር? | | |
| 4 | የትምህርቱ አቀራረብ የተማሪዎቹን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ ነበር? | | |
| 5 | የንግግር ትምህርቱን በበቂ ሁኔታ ይለማመዱ ዘንድ ተማሪዎችን የማነቃቃት ተግባር ተከናውኗል? | | |
| 6 | የቀረቡት መመሪያዎች ለተማሪዎቹ ግልፅ ነበሩ? | | |
| 7 | በልምምድ ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ጉልቶ ይታይ ነበር? | | |
| 8 | ተግባሩን ለማለማመድ የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ ተጠቅመዋል? | | |
| 9 | የንግግር ክሂልን ማለማመድ የሚያስችሉ ተግባራት (በክርክር፣ በጭውውትና በውይይት መልክ) ተከናውነዋል? | | |
| 10 | የንግግር ክሂል ልምምዱን ለማድረግ በግል ፣በጥንድና በቡድን የማስተማር ስነ-ዘዴ ተጠቅመው ነበር? | | |
| 11 | በልምምድ ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሣተፉ ይደረግ ነበር? | | |
| 12 | ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች እንዲለማመዱ ይበረታቱ ነበር? | | |
| 13 | ልምምዱ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይከናወን የተለያዩ ዘዴዎች ይጠቀሙ ነበር? | | |
| 14 | በልምምዱ ወቅት ተማሪዎች እርስ በርስ በመወያየት ልምምድ እንዲያደርጉ ይበረታቱ ነበር? | | |
| 15 | ተማሪዎቹ ያልገባቸውን ጥያቄዎች እንዲያቀርቡ ሰፋ ያለ ዕድል ተሰቷቸዋል? | | |
| 16 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎች ሲሳሳቱ ለመርዳት ጥረት ተደርጎ ነበር? | | |
| 17 | የሚታዩ ስዕሎችና ፎቶግራፎችን በማቅረብ የሚያዩትን ነገር በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ይደረግ ነበር? | | |
| 18 | የንግግር ተግባራቱ ተማሪዎችን በቀላሉ እና በነፃነት ሊያግባባ የሚችል ዐውድ በመፍጠር የተከናወኑ ናቸው? | | |
| 19 | ውይይት እና ክርክር በማዘጋጀት የንግግር ተግባር እንዲከናወን ተደርጓል? | | |
| 20 | ተማሪዎች ስህተት ሲፈጽሙ እርማቱ በወቅቱ ይሰጥ ነበር? | | |

## አባሪ ሁለት

### ጅማ ዩኒቨርስቲ

### ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

### የአማርኛ ቋንቋና ስነ-ፅሁፍ  ትምህርት ክፍል

**የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ**

**የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት  የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ አተገባበር ለመፈተሽ ለ9ኛ ክፍልተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሁፍ መጠይቅ**

**ውድ ተማሪዎች!**

**ይህ መጠይቅ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የንግግር ክሂል አተገባበር በክፍል ውስጥ እንዴት እየቀረበ እንደሆነ ለመፈተሽ የተዘጋጀ ነው። ስለሆነም የምትሰጡት ምላሽ ለጥናቱ የላቀ ድርሻ ስላለው ትክክለኛውን መልስ በመስጠት ትተባበሩኝ ዘንድ እየጠየኩ ለምታደርጉልኝ መልካም ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ።**

**ክፍል አንድ**

አጠቃላይ መረጃ

የትምህርት ቤቱ ስም _______________

ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ዞን______________________ ወረዳ _______

የተማሪው ክፍል ደረጃ _______

ፆታ ወንድ ☐ ሴት ☐

## ክፍል ሁለት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ያለህን/ሽን አመለካከት በትክክል ያመለክታል የምትለውን/ይውን ሀሳብ በቀኝ በኩል ከተሰጡት አማራጮች መካከል አንዱን በመምረጥ የ / √/ ምልክት በማድረግ አመልክት/ች፡፡

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | መወሰን ያቅተኛል | አልስማማም | በፍፁም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የንግግር ትምህርት ክሂልን ተግባር ከማከናወናችሁ በፊት አላማው ይገለፅላችኋል? | | | | | |
| 2 | የንግግር ክሂል ተግባር በክፍል ውስጥ ከመቅረቡ በፊት በተለያዩ መንገዶች መምህራን ያነቃቃሉ? | | | | | |
| 3 | የንግግር ክሂል ተግባር ከመጀመራቸው በፊት አጭርና ግልፅ መመሪያ ይሰጡ ነበር? | | | | | |
| 4 | ዋናውን የንግግር ተግባር ተማሪዎች ከማከናወናቸው በፊት ምሳሌ የሚሆኑ ተግባሮች ይቀርቡ ነበር? | | | | | |
| 5 | በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን ውይይት፣ ወዘተ...በአንድነት በመሆን የንግግር ክሂል ተግባርን በክፍል ውስጥ የማከናወኑ ሁኔታ ነበር? | | | | | |
| 6 | በግል፣ በጥንድ፣በሶስትዮሽ፣ በቡድን፣ ወዘተ የንግግር ክሂል ተግባራትን እንድታከናውኑ መምህሩ እየተዘዋወሩ ያበረታቷችኋል? | | | | | |
| 7 | በክፍል ውስጥ ንግግርን በሪፖርት፣ በጭውውት፣ በክርክር፣ በውይይት መልክ ተግባራቱን መለማመዱ የንግግር ችሎታን አጐልብቷል? | | | | | |
| 8 | በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የንግግር ክሂል ተግባራት ከተማሪው የህይወት ልምድ ጋር የተቆራኙ ናቸው? | | | | | |
| 9 | በጥንድ፣በቡድን ወዘተ በመሆን የንግግር ክሂል ተግባራትን በመለማመድ እና በመከታተል የንግግር፣ የጭውውት ፣ የክርክር የውይይት ሥርዓት እንዲዳብር ተደርጓል? | | | | | |
| 10 | የንግግር ተግባራትን ስታከናዉኑ ሀሳባችሁን በነፃነት እንድትገልፁ ተደርጓል? | | | | | |
| 11 | በጥንድ፣ በቡድን በመሆን ቃለ መጠየቅ ማድረግ፣ ስዕላዊ መግለጫዎች በሚያስተላልፉት ሀሳብ ላይ መወያየትና መከራከር ሀሳብን ያለፍርሀት ለመግለፅ ተችሏል? | | | | | |
| 12 | የጭውውት ፣ የክርክር፣ የውይይት ተግባራት በክፍል ውስጥ ከቀረቡ በኋላ ያለምንም ፍርሀት አስተያየት እሰጣለሁ? | | | | | |
| 13 | ስህተታችን በቀጥታ ከመናገር ይልቅ እርስበርስ እንድንተራረም ይደረግ ነበር? | | | | | |
| 14 | ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች እንዲናገሩ ይበረታታሉ? | | | | | |
| 15 | የንግግር ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል ይሰጣሉ? | | | | | |

# አባሪ ሶስት

## ጅማ ዩኒቨርስቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ

## ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረቡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

ክቡር የ ____________________ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህር ይህ ቃለ መጠይቅ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንግግር ክሂል አተገባበር በክፍል ውስጥ እንዴት እያቀረቡ እንዳለ ለመፈተሽ የተዘጋጀ ነው፡፡ ከመጠይቁ የሚገኘው ምላሽ ለተጀመረው ጥናት መሳካት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ይታሰባል፡፡ ጥናቱ የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ የሙያው ባለቤቶችን ድጋፍ የሚጠይቅ ስለሆነ እርስዎም በዚህ ቃለ መጠይቅ ላይ በመሳተፍ የበኩልዎን ሙያዊ ድጋፍ ያደርጉልኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

በመጨረሻም እጅግ ውድ የሆነ ጊዜዎን ሰጥተው ትብብር ስላደረጉልኝ ምስጋናዬ ይድርስዎ፡፡

ክፍል አንድ፡-የመምህራን አጠቃላይ መረጃ

1. ጾታ ________________________________
2. ዕድሜ________________________________
3. የትምህርት ደረጃ ________________________________
4. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ ____________________________
5. የአገልግሎት ዘመን ______________________________

ቋንቋን በማስተማር ዘዴ ልዩ ሥልጠና ወስደው ከሆነ በምን?

ይግለጹ________________________________________

ክፍል ሁለት፡ የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበር ፍተሻን መሰረት ያደረጉ

የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት  የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች አራት አማራጮች ተሰጥተዋል፡፡ እርስዎም ከአማራጮቹ መካከል መልስ ይሆናል ብለው ያሰቡትን አንድ  አማራጭ ብቻ በቃል ይናገሩ፡፡

1.ሁልጊዜ አቀርባለሁ

2.አብዘኛውን ጊዜ አቀርባለሁ

3.አንዳንድ ጊዜ አቀርባለሁ

4.ጨርሶ አላቀርብም

1. የንግግር ክሂል ትምህርት ከመቅረቡ በፊት ዓላማውን በግልጽ ያቀርባሉ?
2. የንግግር ክሂል ተግባር በክፍል ውስጥ ከመቅረቡ በፊት በተለያዩ መንገዶች ተማሪዎችን ያነቃቃሉ?
3. ከንግግር ክሂል ትምህርት በፊት ስለ ንግግር አቀራረብ ተማሪዎች እንዲያውቁ ያደርጋሉ?
4. ለንግግር ክሂል ትምህርት የሚሆኑ አጋዥ መርጃ መሳሪያዎችን በማምጣት ያስተምራሉ?
5. ተማሪዎቹ በቀረበላቸው ተግባር መሰረት የማስመሰልና የመደጋገም ስራዎችን እንዲያከናውኑ ያደርጋሉ?
6. በክፍል ዉስጥ ለንግግር ክሂል ትምህርት የሚሆኑ ርዕስ ጉዳዮችን በማቅረብ በተማሪዎች የህይወት ገጠመኝ ዙርያ እነዲለማመዱ ያደርጋሉ?
7. ተማሪዎች በራሳቸው የቋንቋ እውቀት ተጠቅመው በመለማመድ ሀሳባቸውን በነጻነት የሚገልጹበትን መንገድ ያመቻቻሉ?
8. አብዘኛውን ጊዜ ለመናገር የማይደፍሩና ሀሳባቸውን ለመግለጽ የሚያዳግታቸውን ተማሪዎች እንዲናገሩ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ያበረታታሉ?
9. የንግግር ክሂል ትምህርትን ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ያስተምራሉ?
10. የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚታዩ ነገሮችን ማለትም ስዕል፣ ቅርጻቅርጽ፣ ካርታዎችን ወዘተ... በመስጠት እንዲለማመዱና እንዲናገሩ ያደርጋሉ?
11. ተማሪዎችን በጥንድና በቡድን በመከፋፈል ሀሳብ ለሀሳብ እንዲለዋወጡ ያደርጋሉ?
12. የንግግር ተግባሩ ከቀረበና በዚያ ላይ ከተለማመዱ ቦኋላ ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ ያበረታታሉ?

13. ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ሰዎችን ጠይቀው ወይም ምልከታ አድርገውና የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ያደርጋሉ?
14. በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት በተማሪዎቹ ንግግር መሀል ጣልቃ በመግባት እንዴት መናገር እንዳለባቸው እርማት ይሰጧቸዋል?
15. የንግግር ክሂል ትምህርቱ ከመጠናቀቁ በፊት ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ የበረታታሉ?
16. ተማሪዎች ስህተትን እንደ አንድ የመማሪያ መንገድ አድርገዉ እንዲቆጥሩ  ያስገነዝቧቸዋል?
17. ተማሪዎች ስህተታቸውን እርስ በእርሳቸው እንዲተራረሙ ያመቻቻሉ?
18. በቀረበው የንግግር ክሂል ትምህርት ላይ የማሻሻያ ሀሳብ ይሰጣሉ?